

# እናንብብ


ነጻ የአማርኛ ዲጅታል መጽሔት

ቅጽ ፩ ቁጥር ፩

ህዳር ፲፬ ፳፻፲፪


## "ስዕል"
ፀጋልጸት መስሎቅ

## " የስኬት ፍርሃት"
ዶር እዮብ ማሞ

## "የአማርኛ (ኢለማዊ ) ስነ ጽሁፍ አጭር ታሪክ"
ቴዎድሮስ ሸዋንግዛው

## "ረቡኒ "
ነብሙሉቀን ሶ•

## "አንድ ቀን አንት ነው?"
በላይ በቀለ ወያ

# አቡጊዳ ግራፊክስ

DEREJE AND TOLOSA

HOLLYWOOD
MOVIE GALLERY

ኑ ሚዲያ

The Ethiopian
Economist View

ኑ እናንብብ
ነጻ የአማርኛ ዲጅታል መጽሔት | Free amharic Digital Magazine

0970514616
0901062515

ሀሳብዎን እንገልጻለን !
We Make Your Thout !

# በዚህ ዕትም




፨ የአዘጋጁ መልዕክት
ገጽ - ፩



፨ ሌዕል
ገጽ - ፫–፯




፨ ዐውዳ ግጥም
ገጽ - ፰ ፡፲፫ ፡፳



፨ አዕምሮ
ገጽ - ፱



፨ ልቦወለድ
ገጽ - ፲–፲፮




፨ ቅምሻ
ገጽ - ፲፪ - ፲፩



፨ ጥቆማ
ገጽ - ፲፯



፨ ወግ
ገጽ - ፲፰–፲፱

ዶጽሁፍ ለእግዚአብሔር ልጆች
(A Message to the children of God)

፨ ገጾች
ገጽ - ፳፮ - ፳፯

አዲስ ለንባብ የበቁ መጽሀፍት

፨ የመጻህፍት ዳሰሳ
ገጽ - ፳፮ - ፳፯

ኑ እናንብብ
ነጻ የአማርኛ ዲጂታል መጽሔት | Free amharic Digital Magazine

አቡጊዳ ግራፊክስ
@abugida_graphic

# የአዘጋጁ መልዕክት

ውድ የኑ እናንብብ መጽሔት አንባብያን ይህች የመጀመሪያ እትማችን ናት፡፡ ይህች መጽሔት በስፋት የምትዳስሰው ጥበባዊ ሥራዎችን ነው፡፡
የ በይነመረቡን (Internet) ወጣት ወደ ንባብ አለም ለማስገባትና በተለይ ወጣቱ የንባብ ልምድ እንዲኖረው የበኩሏን ድርሻ ለመወጣት አህዱ ብላ የምትጀምር ወርሃዊ መጽሔት ነች፡፡
ኑ እናንብብ ጥሪ ነው! ለሁላችንም፡፡መጠነኛ ልምድ ካላቸው/ጀማሪ/ እስከዳበረ የንብብ ክህሎት እስካላቸው እንዲሁም፤ከጀማሪ ፀሀፍት ለምድ እስካካበቱ ሁሉ የመጥሪያ ደውል እንድትሆን ለሁሉም ቀርባለች፡፡ሚዛናዊ እና የሰለጠነ አስተሳሰብ ያለውን ትውልድ ለማፍራት ንባብ አይነተኛ ሚና አለው፡፡
ስለዚህ መጠነኛ እና የዳበረ የመጻፍ ልምድ ያላቸው የሚታዩበት፤ጀማሪ አንባቢያን እውቀት የሚቀስሙበት፤በሳል አንባቢያን ሂስ የሚሰጡበትን መድረክ መፍጠር አላማዋ አድርጋ የተነሳች መጽሔት ናት፡፡ሀሳብ አስተያየትዎ ያበረታናል እና መስተካከል ያለባቸውን በመጠቆም ያበርቱን፡፡

መልካም ንብብ!

**ዋና አዘጋጅ**
ዮናስ ኃ/ማርቆስ

+251 970514616
lijyoha@gmail.com
Yonas H markos

**የመጽሔት ዲዛይን አቡጊዳ ግራፊክስ**
ዮናስ ኃ/ማርቆስ

+251 970514616
lijyoha2@gmail.com
Yonas H markos

**አርታኢ**
የምስራች ፀዳለብርኃን

+251 901062515
letsreadM@gmail.com


የ ፀጋልደት ምስሎች



Tsegalidet Paintings


Tsegalidet Paintings

ከሙሉቀን ሰ•

# ረቡኒ

በ ላ   ል በ ል ሀ

ያልሰራውን ታሪክ — በትጋት ሚያፈርሰው
ምሁር አይደለም ወይ — ሀገር የሚያምሰው
? ? ?
ሰውነትን ረስቶ
በጎጥ ሚያሳድድሽ — በብሔሬ ሚመታኝ
ዶክተር አይደለም ወይ
ይኽ ሁሉ ዘረኛ — ይኼ ሁሉ ተንታኝ
? ? ?
ከጦርነት ይልቅ — በፍቅር ሚያስጠራት
ጠቢብ አይደለም ወይ — ሀገሬን ያጠራት
? ? ?
ሀገር ተጠየቂ
ሳይወጣ በዱላ — በሀፍረት ሚያኮስስሽ
ሲመረቅ በቃላት — ሚፈረካክስሽ
ባለቆብ አይደል ወይ — የሚያተራምሰሽ
? ? ?
እንጂማ
ሲያሻን ምናሰፋው — ሲያሻን ምናጠበው
አንጡራ ሀብቱን ዘርፈን — በስድብ ምናጥበው
የሰውነት ግብር
ከሰው ልጅ ቀለም ጋር — የማይምታታበት
ሌላውን ማክበሩ
ከራሱ ክብር ጋር — የማይጋጭበት
ቀዬውን መውደዱ
ከሀገሩ ፍቅር ጋር — የማይጣላበት
ሰጥተነው የማናውቅ — የምንጠብቅበት

ጥልቅ ነው ሰፊው ህዝብ
ዝምታው ሚያስፈራ — አንደበቱ ያማረ
ትምህርት ቤት ልኮህ — ከህይወቱ የተማረ

እናም
አያውቅም ምትሉት — አዋቂዎች ሁሉ
ጥበብ ጎድሏችኋል — እንኩ ተካፈሉ
መሀይም ሚለውስ — ምሁሩ የታለ
ይምጣና ይመልከት — መምህር የት እንዳለ

ከአለመማሩ ላይ — እውቀት ሚያካፍልህ
ከተማረ ሚሻል — ያልተማረ አለልህ

ከአለማወቁ ላይ — ጥበብ ያካፈለ
መማርን የሚያስንቅ — አለመማር አለ፡፡




# የስኬት ፍርሃት

ይህ ፍርሃት ለብዙ ሰዎች ግር የሚል የፍርሃት አይነት ነው፡፡ "ሰው እንዴት መሳካትን ይጠላል፣ እንዴትስ ያስፈራዋል?" ሊያስብልም ይችላል፡፡ ይህ ፍርሃት ግን ለፍርሃቱ ሰለባ ለሆኑ ሰዎች እንኳ በግልጽ እንደፍርሃት በማይታወቅበት መልኩ ብዙ ሰዎችን ያጠቃል፡፡

ይህ ፍርሃት ካለመሳካት ፍርሃት ጋር በጥቂቱ ይዛመዳል፡፡ የዚህ ፍርሃት ሰለባዎች ከተሳካላቸው በኋላ እንደገና ወደአለመሳካት የመምጣትን ሁኔታ በመፍራት ይጠቃሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ያሉበት ሁኔታ ምንም የወረደ ቢሆንም እንኳ በዚያ በመደላደል ምንም ለውጥን ያለመፈለግ አመለካከት ይጫናቸዋል፡፡ በተጨማሪም፣ ከስኬት ጋር የሚመጣውን የሰዎችን ትኩረት የማግኘት ሁኔታ፣ ዝናን፣ በስኬታቸው የሚቀኑ ሰዎችን ሁኔታና የመሳሰሉት ሁኔታዎች በጥብቅ ይፈራሉ፡፡ከተሳካልኝ ሰዎች ከእኔ የሚፈልጉት ነገር ይበዛና መቀያየም ውስጥ እገባለሁ የሚልም ስጋት ሌላው ምልክት ነው፡፡ ስለዚህም በስራ፣ በንግድ፣ በትምህርትና በመሳሰሉት ነገሮች ዘልቆ መሄድ ያስቸግራቸዋል፡፡

ለማስታወስ ያህል ...

- ስኬተ-ቢስ ከመሆን ስኬታማ መሆን በብዙ ይመረጣል፡፡
- ስኬታማ ሰው መሆን ማለት ሁሉም ነገርህ እንቅፋት የማያገኘው ይሆናል ማለት አይደለም፡፡
- የማንነትህን ተመን ከስኬታማነትህ አንጻር ከማውጣት ተጠበቅ፡፡
- ስኬታማነት አመለካከትህን በትእቢት ወደ ላይ ካላወጣው፣ ስኬት ማጣት ወደ ታች ሊጥልህ አይችልምና አመለካከትህን ጠብቅ፡፡
- ስኬታማ ብትሆን የየትኛውን ሰው፣ ቤተሰብ ወይም የሕብረተሰብ ክፍል ልትጠቅም እንደምትችል አቅድ፡፡

ቲክቫህ ኢትዮጵያ
ቲክቫህ ኢትዮጵያ ታማኝና ፈጣን የዜና ምንጭ ነው፡፡
እንዲሁም የቴሌግራም ቻናላቸውን በመጠቀም
የበጎ አድራጎት ስራ እየሰሩ ይገኛል፡፡የኛንም መጽሔት በቻናላቸው
በመልቀቅ ላደረጉልን እገዛ እናመሰግናለን፡፡

የቲክቫህ ኢትዮጵያን
ቴሌግራም አድረሻ ለማግኘት
እዚህ ይጫኑ

ቃኪዳ ተሸመ

# እፀልይልሃለሁ

[ ... ትፀልይልኛለች ። በጧት ፡ እንደመነሳት ፡ ነው ። ፀሎትና ፡ ጊዜ ፡ መልካቸውን ፡ ለማሰናሰል ፡ ይጥራሉ ። ለፀሎቷ ፡ ጧቷን ፡ ትናፍቃለች ። ለመተኛት ፡ ከምታደርገው ፡ ፀሎት ፡ በላይ ፡ ጧት ፡ ላይ ፡ የምታደርገው ፡ ይረዝማል ። እንቅልፍ ፡ የሚወስዳት ፡ ሳፀልይ ፡ ውሎዋ ፡ የሚመሽላት ፡ አይመስላትም ።

በጊዜ ፡ ሒደት ፡ የተረዳሁት ፡ የኔን ፡ የመፀለይ ፡ መንፈስ ፡ ወስዳዋለች ። በእሷ ፡ ፀሎት ፡ መብቃቃትን ፡ ለምጃለሁ ። ከሁሉም ፡ ከሁሉም ፡ የጓደኛ ፡ ፀሎት ፡ ደራሽነቱን ፡ አማኙ ፡ ልቤ ፡ ይመሰክራል ። ስትፅልይ ፡ ትመጠናለች ። የመሰልከክ ፡ መልክ ፡ ትላበሳለች ። ታምራለች ።

... የአንባሻ ፡ ዳቦ ፡ ወረፋ ፡ ጥበቃ ፡ ላይ ፡ ተዋወቅኳት ። የኾነ ፡ ግራጫማ ፡ ማለዳ ፡ ነው ። ብሩህነት ፡ የሌለው ... የኾነ ፡ ድብርታም ... አገጫምም ፡ ነበር ። የለበሰችው ፡ ሺቲ ፡ በግልገል ፡ ሱሪዋ ፡ አፍ ፡ ውስጥ ፡ በመልክ ፡ ተወትፏል ። ሸብ ፡ ያደረገች ፡ ሻሽ ፡ የጉራጌ ፡ ሙዚቃ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ተወዛዋዦች ፡ መሐል ፡ ቆንጆዋን ፡ አስመስሏታል ( እዚህ ፡ ሐሳብ ፡ ውስጥ ፡ ኾኜ ፡ ለመጨፈር ፡ ቃጥቶኛል )። ፊቷን ፡ ታጥባ ፡ በሩጫ ፡ እንደመጣች ፡ ፊቷ ፡ ላይ ፡ ቅርዝዝ ፡ ብለው ፡ ለመኩለል ፡ የሚያዘግሙት ፡ የውሃ ፡ ዘለላዎች ፡ ያሳብቃሉ ። የመልኳ ፡ ቀለም ፡ አይከብድም ። ከቁንጅናዋ ፡ ላይ ፡ የፈሰሰው ፡ ደምግባቷ ፡ ልብን ፡ ያሳሳል ። የመጀመሪያ ፡ ዕይታዬ ፡ እንደማይዋሸኝ ፡ አምናለሁ ። ለተመስጥኦ ፡ ቦታ ፡ ይከፍትልኛል ። ጀሃነም ፡ የምገባው ፡ በዐይኔ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ አስባለሁ ። ከዚያ ፡ አስባለሁ ። እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ፈጥሮ ፡ ዐትዩ ፡ ምንኛ ፡ ነው? ይሔ ፡ መልክ ፡ ላይ ፡ ትኩረት ፡ ዋጋ ፡ አለው ። “ወይኔ ፡ ስታምር!” በሚል ፡ ቃል ፡ አያልቅም ። በዕይታዬ ፡ ጨረስኩ ። አንባሻውንም ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ይዤ ፡ ገብቼ ፡ በመልኳ ፡ አወራረድኩት በሐሳብ ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ መመገብ ፡ ተስማሞቱና ፡ ተዝናኖቱ ፡ በቃል ፡ አይገለፅም ። የመንፈስ ፡ ምግብም ፡ ይኾናል ።

በተደጋጋሚ ፡ አንባሻ ፡ በላሁ ። አንባሻ ፡ ያግባባል ። መቃጠሪያ ፡ ይኾናል ። ተግባባን ፡ ብዙ ፡ ብዙ ፡ አንባሻ ፡ ቁመን ፡ ጨረስን ። እሷ ፡ ትፀልያለች ። ረዥም ፡ ፀሎት ። ታነበንባለች ፡ በማይገባኝ ፡ ቋንቋ ... ዐይኗን ፡ ጨፍና ፡ ስታነበንብ ፡ እኔ ፡ እሽሞነሞናለሁ ። ከናፍሯ ፡ ሲንቀሳቀስ ፡ ምን ፡ ለማድረግ ፡ እንደፈለኩ ፡ እየገባኝ ፡ የማደርገው ፡ ይጠፋኛል ። ደሞ ፡ ማድረግ ፡ የፈለኩትን ፡ ድፍረቴ ፡ ይቀማኛል ። ‘ደፋርና ፡ ጭስ ...’ ብሎ ፡ ተረት ፡ ቀለለብኝ ። ደፋር ፡ መውጫ ፡ እንጂ ፡ ከመውጪያ ፡ በላይ ፡ መግቢያውን ፡ አያውቅም ።

እሷ ፡ ትፀልያለች ። እኔ ፡ አስባለሁ ። የማሰብና ፡ የመፀለይ ፡ ልዩነታቸው ፡ ምንድን ፡ ነው? መፀለይ ፡ ከየዋህነት ፡ ጋር ፡ ዝምድና ፡ አላቸውን? ስትጨርስ ፡ ከዝምታ ፡ ተነስታ ፡ ወደ ፡ ሞቀ ፡ ፈገግታ ፡ ትገባለች ። ትነፃለችም ። የውበቷ ፡ መጎምራት ፡ የመፀለይዋ ፡ ትሩፋት ፡ ይመስለኛል ። ከዚያ ፡ የመጀመሪያ ፡ ቁርሻዋን ፡ ታጎርሰኛለች ። ታስቀድመኛለች ።

ጉርሻ ፡ የማቀራረቡ ፡ ኃይል ፡ ይገርመኛል ። ለሌላ ፡ መሳሳትን ፡ ያላብሳል ። በስልክ ፡ ከድምጿ ፡ ጋር ፡ ተዋህጃለሁ ። ትደውልልኛለች ።

ከማውራታችን ፡ በፊት ፡ ትፀልያለች ።
አደምጣታለሁ ።
እናወራለን ።
ከዚያ ፡ ትፀልያለች ።
እንጨርሳለን ።
ፀልያ ፡ ትዘጋለች ።
“ እፀልይልሃለሁ! “ ትላለች ።

በፀሎቷ ፡ የቆየሁ ፡ ይመስለኛል ። ምንድን ፡ ነው ፡ የምትፀልይው ፡ ብዬ ፡ ለመጠየቅ ፡ ያሰብኩበት ፡ ቀን ፡ የለም ። ትዝም ፡ አይለኝ ። ስትፀልይ ፡ ስለምትፀልየው ፡ ነገር ፡ በላይ ፡ ፀሎቷ ፡ ፊቷ ፡ ላይ ፡ የሚያረብበው ፡ መንፈስ ፡ በተዝናኖቷ ፡ መልስ ፡ አገኛለሁ ።

... የመጀመሪያ ፡ ምሽት ፡ በቀዝቃዛው ፡ ዐየር ፡ ውስጥ ፡ ታሞቀኛለች ። ስንገናኝ ፡ ፀለየች ። ወጋችንን ፡ እንወገውጋለን ። ጨዋታ ፡ ላይ ፡ ተጫዋች ፡ ነኝና ፡ እንጫወታለን ። በጫወታ ፡ ውስጥ ፡ መግባባት ፤ መዋደድ ... ከጫወታችን ፡ ተገለን ፡ ተቃቅፈን ፡ ከጦሳ ፡ አናት ፡ እየከነፈ ፡ የሚመጣውን ፡ ዐየር ፡ ማድመጥ ፡ ተያያዝን ። ለስላሳ ፡ ጠረኗ ፡ ከንፋሱ ፡ ጋር ፡ እየተንቦለቦለ ፡ ዐየሩን ፡ ለኛ ፡ ድምቀት ፡ ኾነ...

ከሠፈራችን ፡ ራቅ ፡ ብለን ፡ ካለ ፡ ብሳና ፡ ዛፍ ፡ ስር ፡ ቆምን ። በዚያ ፡ ገርበብ ፡ ባለ ፡ ብርሐን ፡ እንተያያለን ። ዐየሩ ፡ ብርሐኑ ፡ ሙቀታችን ፡ ያሳስበናል ። እንተያያለን ። መሳሳባችን ፡ በከንፈሮቻችን ፡ እንድንደባበስ ፡ ጋበዘን ። ተጠጋጋን ። ስንጠጋጋ ፡ በጆሮየ ፡ ከሚሞቅ ፡ ትንፋሿ ፡ ጋር ፡ ተደምሮ ፡ እንዲህ ፡ አለችኝ ።

" እንፀልይ! "

ሠውነቴን ፡ በሞላ ፡ ሳቅ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ። በፅድቅ ፡ ዓለም ፡ የገባሁ ፡ መሰለኝ ። ጀነት ፡ ከዚህ ፡ እንደማትርቅ ፡ ባምንም ፡ በቅርቡ ፡ እንደምንዋዋል ፡ አልገመትኩም ። የምፀልየውን ፡ ነገር ፡ ባስበው ፡ ከሳቅ ፡ መንደር ፡ ውስጥ ፡ ይከተኛል ። ስቆ ፡ መሳም ፡ ይቻላል?

"ዐይናችንን ፡ እንጨፍን?"

ጨፈንኩ!

ምን ፡ ምን ፡ እንደምል ፡ ባላውቅም ፡ ጨፈንኩ ። የመሳም ፡ ኃይል ፡ ልዩ ፡ መኾኑን ፡ ባውቅም ። ዐይንን ፡ ገልጦ ፡ መሳም ፡ አለመቻሉን ፡ አውቃለሁ ። መጀመሪያ ፡ ጨፍኖ ፡ ፀልዮ ፡ አንደገና ፡ ወደ ፡ ከንፈር ፡ ማዕበል ፡ ጋር ፡ መላተም ፡ እንዴት ፡ ይኾን?

የከንፈሯ ፡ እንቅስቃሴ ፡ ከጆሮዬ ፡ ሰፈር ፡ ድርስ ፡ ኮቴው ፡ ይሰማል ። ተዐምር ፡ ውስጥ ፡ እየተኖኃለልኩ ፡ ነው ። መጨረሷን ፡ በእሷ ፡ እረፍት ፡ ይቃኛል ።

ዐይኔን ፡ መግለጥ ፡ ጠላሁ ።

ተጠጋችኝ ፡ ተጠጋኋት ።

በከንፈሯ ፡ ዳሰሰችኝ ። ተለሳለስኩ ። መፍረስ ፡ አማረኝ ። ትንቡክቡክነት ፡ ሰውነቴ ፡ ውስጥ ፡ ሰረፀ ... ያ ፡ "ቂጤን ፡ ጨብጭልኝ" ባይ ፡ ልጅ ፡ በትዝታ ፡ ጠራኝ ። ያለበት ፡ ሚስጥር ፡ ባይገለጥልኝም ፡ ሚስጥሩን ፡ ቢገልጥልኝ ፡ ወደድኩ... መጨረሻው ፡ ምን ፡ ነበር?

ትንፋሼን ፡ ሰብስቤ ፡ ጠየቅኋት ።

ፊቷ ፡ ቲማቲም ፡ መስሏል ።

ምን ፡ እንዳደረኩላት ፡ አልገባኝም ።

"መፀለይ ፡ አማረኝ?" የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ጠየቅኋት ። አካባቢው ፡ ዳሎልን ፡ ተላብሷል ። መልከዓ–ምድሩ ፡ ጀነትን ፡ ተማስሏል ። በከናፍሯ ፡ ዐይኗን ፡ ጨፍና ፡ ሽምዜን ፡ ጨምድዳ ... እንዲህ ፡ አለችኝ ፡ ከናፍሮቿን ፡ ከናፍሬ ፡ ላይ ፡ አንተርሳ ፤ ተንተርሳ ።

፧

" እፀልይልሀለሁ! " ... ]

ኑ እናንብብ
ነጻ የአማርኛ ዲጅታል መጽሔት|free Amharic Digetal Magazine
ለሀሳብ አስተያየት
+251 970514616
+251 901062515

# የአማርኛ (አለማዊ) ስነ ጽሁፍ አጭር ታሪክ

ቴዎድሮስ ሸዋንግዛው

## የአማርኛ (አለማዊ)ስነ ጽሁፍ አጭር ታሪክ — ክፍል አንድ

የኢትዮጲያ አማርኛ ስነ ጽሁፍ በብዙ ምክንያቶች በአፍሪካ ውስጥ ለየት ብሎ ይታያል።በቅድሚያ የክፍለዘመናት እድሜ ካለው፣ ቱባ ባህል ብዙ እሴት ይመዛል።ቀጥሎ አውሮፓውያን አፍሪካን በሚቀራመቱበት ዘመን፣ ኢትዮጲያ ብቸኛዋ ነጻ ሀገር ሆና በመቀጠሏ ከውጪው አለም ወጀብ ተጠብቃ ኖራለች።በመጨረሻም ኢትዮጲያ በአፍሪካ ውስጥ የራሷ ፊደል ያላት ብቸኛዋ ሀገር ናት።በነዚህ ምክንያቶች የተነሳ በዋነኝነት አፍሪካዊ በሆነ ቋንቋ ካሉ ስነ ጽሁፎች፣ የኢትዮጲያ በብዛትም በጥራትም ይልቃል።ከልማዳዊውና መንግስታዊ ጉዳዮችን ሁሉ በግዕዝ ከመጻፍ ተላቅቆ፣ በአማርኛ እንዲተካ ፈር የቀደደው ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስ በኢትዮጲያ እንዲያበቃ ያደረገው ዘመነ መሳፍንትን ብቻ ሳይሆን ዘመነ ግዕዝን ጭምር ነው።የትግሬው ንጉስ ዮሀንስ አራተኛም፣ ዙፋኑን ሲረከብ ይኸው አሰራር ዘልቋል።አማርኛ የስነ ጽሁፍ ቋንቋ ሆኖ በደንብ የጸናው ግን፣ የመጀመሪያውን የህትመት መሳሪያ በኢትዮጲያ በተከለው ምኒልክ ሁለተኛ ግዜ ነበር። (እነዚህ ሶስት ንጉሶች የኢትዮጲያን የስልጣኔ ኳስ በአግባቡ ሲቀባበሉ የነበረ ይመስለኛል) የመጀመሪያው የኢትዮጲያ ጋዜጣ የሆነው አእምሮ መታተም የጀመረውም በዘመነ ምኒልክ ነበር።በቀዳማዊ ሀይለስላሴ የግዛት ዘመን ደግሞ አማርኛ ከአለማዊ ስነ ጽሁፍ ባሻገር ወደ ቤተ ክርስቲያንም ተስፋፋ፤ለምሳሌ ያህልም የቅድስት ስላሴ ካቴድራል በግዕዝ ፈንታ አማርኛን ለመዘሙር አገልግሎት ትጠቀምበት ነበር።የመጀመሪያው የአማርኛ ልብወለድ የታተመውም አፈወርቅ ገብረየሱስ በ1908 ጦቢያ የተሰኘውን የፍቅር ታሪክ ሲጽፉ ነበር።በመቀጠልም ወደ ሀያ የሚጠጉ የህሩይ ወልደስላሴ ጉልህ ስራዎች ብቅ አሉ።ብዙም ሳይቆይ ሀዲስ አለማየሁን የመሳሰሉ ምሁራንም ተውኔቶችን መጻፍ ጀመሩ።ስለ ንጉሳውያን ቤተሰብ ይጽፉ የነበሩት ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሀንስ እና ልብወለዶችን እንዲሁም በእውነተኛ ክስተቶች ላይ የተመሰረቱ ታሪኮችን ይጽፉ የነበሩት መኮንን እንዳልካቸው በቀድሞው ዘመን ከነበሩት ቀደምት ጸሀፍት መካከል ይገኙበታል።አቶ መኮንን የጻፉት "አለም ወረተኛ" የተሰኘ የመጀመሪያ ልብወለዳቸው፣ በጣም ከተወሳሰበ የኢትዮጲያ ቤተሰባዊ እሴቶች ጋር ለመጣጣም ስትል፣ የስቃይ ህይወት ስለምትገፋ አንዲት ሴት ይተርካል። ሁለተኛ ስራቸው በጣሊያኖች እጅ ሰማእት ስለሆኑት አቡነ ጴጥሮስ የሚያወሳ የደም ድምጽ የተሰኘ ተውኔት ነው።የድሆች ከተማ በተባለ ሌላ ልብወለድ፣ ደራሲ መኮንን በራሱ ህልምና ከሰው በተገኘ ጥሩ ምክር መሀል ስለተወዛገበ አንድ ሀብታም ሰው ውስጣው ግጭት ይመረምራሉ።አቶ መኮንን መልካም ቤተሰቦች ብለው የሰየሙትን ግለ ታሪካቸውንም ጽፈዋል።ፈርቀዳጅና የተወሳሰበ እንዲሁም አለም አቀፍ ደረጃ ያለውን አርአያን ደግሞ ደጃዝማች ግርማቸው ተክለሀዋርያት ይዘው ብቅ አሉ፤ በብዙ አለምአቀፍ ቋንቋዎችም ተተረጎመ። ይህ ልብወለድ በ1890ዎቹ የከፍተኛ ትምህርታቸውን በውጭ ሀገር እንዲማሩ በምኒልክ ተመርጠው ከተላኩ በጣት ከሚቆጠሩ ተማሪዎች መሀከል አንዱ በሆኑት የደራሲው አባት ፊታውራሪ ተክለሀዋርያት የህይወት ታሪክ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነበር። ተክለ ሀዋርያት በፍቅር የወደቁላትንና ጋብቻ የምትፈልገውን የራሽያ አሪስቶክራቲክ ወጣት አግብቶ ከውጪ በመቆየትና የኮሎኔሊያዝም ጥላ እያጠላባት ወደነበረው ሀገራችን በመመለስ መሀል ነፍስና ስጋቸው ለውሳኔ ተጨንቃ ነበር። በጉዳዩ ብዙ ከተጨነቁበት በኋላ ወደሀገራቸው ለመመለስ ይወስናሉ፤ስር ሰዶ የጠበቃቸው ልማዳዊው የፊውዳል ስርአት ተስፋ አስቆረጣቸው እንጂ ግርማቸው በመቀጠል ቴዎድሮስ የተሰኘ ተውኔት ጻፉ፤ ይህ ተውኔት ስማቸው ጠልሸቶ የቆየውን የዳግማዊ ቴዎድሮስ እውነተኛ መልክ ለማሳየት ይሞክራል።ቀደምት ኢትዮጲያውያን የታሪክ ጸሀፊዎች የንጉሱ ጨካኝነት ላይ ሲያተኩሩ፣ ግርማቸው በበኩላቸው ቴዎድሮስ በዘመነ መሳፍንት ተንሰራፍቶ የነበረውን ስርአተ አልበኝነት እንዲያበቃ የተጫወቱትን ጉልህ ሚናና አገሪቱን አንድ ለማድረግ ያደረጉትን ብርቱ ትግል ያሰምሩበታል።በቀዳማዊ ሀይለስላሴ የግዛት ዘመን ማብቂያ አካባቢ፣ ግርማቸው ኢትዮጲያ በጣሊያን ላይ ስለተቀዳጀችው ታላቅ ድል የሚያወሳ አድዋ የተሰኘ መጽሀፍም ጽፈዋል። —AFRICA IN FOCUS | ETHIOPIA | PAULOS : MILKIAS | 2011 | PAGES304 - 305

## የአማርኛ (አለማዊ) ስነ ጽሁፍ አጭር ታሪክ — ክፍል ሁለት

ከበደ ሚካኤል ተውኔቶችን ከመጻፋቸው ባሻገር፣ ሀገርኛ አፈታሪኮችን ወደ ስነጽሁፍ በመቀየር ዘላለማዊ አድርገዋል።ሰፋ ያለ አመለካከት ያልነበረውን ኢትዮጲያዊ ተደራሲም፣ ከአውሮፓ ፍልስፍና አስተዋውቀዋል።ሌላ ትኩረታቸውን የሚስብ መስክ ስነ ልቡና ነበር።የከበደ ሚካኤል ግጥሞች በባህሪያቸው አስተማሪነት ይገንባቸዋል፤ ለተግባራዊ ህይወት የሚጠቅም እውቀት እና የግብረገብ መርሆችም በጉልህ የሚታዩ የታሪኩ አካሎች ናቸው።ተራኪ ግጥሞቻቸውም ሰውኛ ዘይቤን በብዛት ይጠቀማሉ (ይህ ዘይቤ እንስሳትና ህይወት የሌላቸው ነገሮች ፍቃድ፣ስሜት፣ቀናነትና ሌሎችንም ሰውኛ ባህሪዎች ተላብሰው የሚታዩበት ነው) ከበደ የመጀመሪያ ስራቸው በ1941 የታተመው ብርሀነ ህሊና የተሰኘ የግጥሞች ስብስብ ነበር።ታሪክና ምሳሌ (1942) ከተፈጥሮ የሚታይ የተለመደ ሁኔታን፣ከሩቅ ከተቀዳ ምሳሌ ጋር በንጽጽር የሚቀርብበት መድብል ነው።ከበደ በመቀጠል በቀዳማዊ ሀይለስላሴ ንጉሳዊ ትእዛዝ የክሌይን Beyond Pardon ከይቅርታ በላይ ብለው ለኢትዮጲያ ባህል በሚስማማ መልኩ ተርጉመዋል።ትልቁ አስተዋጽኦዋቸው ግን በተውኔት ጽሁፍ ነበር።ከታወቁ ተውኔቶቻቸው መሀከል የትንቢት ቀጠሮ (በእግዚአብሔር አለማመንን የሚያጣጥል ሀይማኖታዊ ድራማ) ፥ አቶ በላይነህ ወይም የይቅርታ ማዕበል (ቁሳዊነትንና አለማመንን እንደ ፍጹም ክፋት የሚያሳይ) ፥አኒባል (የሮማንና ካርቴጅን ጦርነት ለኢትዮጲያ ታሪክ እንደ ምሳሌ የሚያቀርብ) እና >>

አጼ ካሌብ(ደቡብ አረቢያ በሚገኙ የክርስትና ጠላቶች ላይ ድል ስለተቀዳጀው ዝነኛው የ6ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአክሱም ንጉስ ካሌብ የህይወት ታሪክ)ይገኙበታል።እንደ ሆሜር፥ዲሞስቴን፥ታላቁ እስክንደር የመሳሰሉ ታላላቅ ሰዎችን ታሪክም ለአማርኛ አንባቢ አቅርበዋል።ከትርጉም ስራዎቻቸው መሀከል የሼክስፒር ሮሜዎና ጁሌት አንዱ ነው።ምእራባዊነትን ወደ ባህላዊ ማህበረሰብ ማምጣት ጽኑ ምኞታቸው የነበረውን የቀዳማዊ ሀይለስላሴን ህልም ለማስረገጥ ጃፓን እንደምን ሰለጠነችን በ1953 ጽፈዋል።ራስ እምሩ ሀይለስላሴ ከአሪስቶክራት ወደ ተራማጅ የተቀየሩ ጸሀፊ ነበሩ።እምሩ ፊታውራሪ በላይ የተሰኘ ታሪካዊ ልብወለድ፥ሰውና እውቀት(Epis-temology የተሰኘውን የፍልስፍና ዘርፍ ደራሲው በተረዱት መልኩ የሚያስተነትኑበት)፥አለምና ትግል(የሰውን ልጅ አለማዊ ፈተና የሚያሳይ)ጽፈዋል።ካለባቸው የአስተዳዳሪነት ሐላፊነት ጎን ለጎን ስነ ጽሁፍን ስራዬ ብለው ከያዙ የሀይለስላሴ ባለስልጣኖች መሀከል ሀዲስ አለማየሁ ዋነኛ ተጠቃሽ ናቸው።የመጀመሪያ ስራቸው የሀበሻና የወደሏላ ጋብቻ የተሰኘ ተውኔት ነበር።ተውኔቱን የጻፉት በጣም በልጅነታቸው ገና የአንደኛ ደረጃ ተማሪ ሳሉ ነበር።ተውኔቱም ኢትዮጲያ በጣሊያን ከመወረሯ 5 አመት አስቀድሞ ታላላቅ እንግዶች በታደሙበት ቀርቧል።11 ኢትዮጲያዊ ተረቶች ያካተቱበትን ተረት ተረት የመሰረት ቀጥለው ጽፈዋል።ትምህርትና የተማሪ ትርጉም በተሰኘ መጽሀፋቸው የትምህርትን መሰረታዊ አላማ ያስረዱበታል።በጣም ዝነኛ ያደረጋቸው ልብወለድ ታሪክ ግን ፍቅር እስከ መቃብር ነው፤ልቦለዱ ያዘላቸው የትየለሌ ምጸታዊ ይዘቶቹ በኢትዮጲያውያን ዘንድ ተወዳጅነቱን አስተማማኝ አድርገውታል።በሀገሪቱ ውስጥም በብዛት የተሸጠ ዋነኛው መጽሀፍ ሳይሆን አይቀርም።ደራሲው በ1969 የሀይለስላሴን ሽልማት ያሸነፉትም በዋነኝነት በዚህ መጽሀፍ የተነሳ ነው።ከሀዲስ ሌሎች ልብወለዶች መሀከል ወንጀለኛው ዳኛና የልምዣት ይገኙበታል፤በተጨማሪም በህዝብ አስተዳደርና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይም ጽፈዋል።ለኢትዮጲያ ምን አይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል፥በኢትዮጲያ የፖለቲካና ህዝብ አስተዳደር ተማሪዎች ዘንድ በስፋት ተነቧል።በጎጃም፥በአዲስ አበባና በሙሶሎኒ የጣልያን እስር ቤት ያሳለፉትን ህይወት በስፋት የሚተርከው ትዝታ የተሰኘ ግለ ታሪካቸው በኢትዮጵያዊ አንባብያን ዘንድ በፍጥነት ተወዳጅ ሆኗል።አቤ ጉበኛ በአንድ ወቅት በብዛት ይነበብ የነበረ ደራሲና ጸሀፊ ተውኔት ነበር።መጽሀፎቹን ተወዳጅ ያደረጋቸው በሀይለስላሴ ፊውዳላዊ ስርአት ላይ ይሰነዝራቸው የነበሩ የሰሉ ግን ቀጥተኛ ያልሆኑ ሂሶች ነበሩ።የሮም አወዳደቅ የተሰኘ የመጀመሪያው ተውኔቱ ለፊውዳል ስርአቱ ታማኝ አባሎች አካሄዳቸቸውን ካላስተካከሉ እንደሮም ሴናተሮች ክፉ እጣ እንደሚገጥማቸው የሚያስታውስ፥ቀጥተኛ ያልሆነ ማስጠንቀቂያ ነበር።የፓትሪስ ሉሙምባ አሟሟት ቅኝ አገዛዝንና እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝን የሚተች ሌላ ተውኔት ነው።በማህበረሰቡ ውስጥ ተንሰራፍቶ በሚጠብቀው የፍትህ መጓደልና ህሊናቢስነት ምክንያት የእናቱን ማህጸን አልለቅም ስለሚል ህጻን የሚተርከው ምጸታዊ ልብወለድ አልወለድም፥ ያለጥርጥር የደራሲው በጣም ታዋቂ ስራበማህበረሰቡ ውስጥ ተንሰራፍቶ በሚጠብቀው የፍትህ መጓደልና ህሊናቢስነት ምክንያት የእናቱን ማህጸን አልለቅም ስለሚል ህጻን የሚተርከው ምጸታዊ ልብወለድ አልወለድም፥ ያለጥርጥር የደራሲው በጣም ታዋቂ ስራ ነው።

ነው።የፊውዳል ስርአቱን በብርቱ የሚጠዘጥዘውን ይህን መጽሀፍ፥ 800 ቅጂ ብቻ እንደተሸጠ መንግስት የተቀረውን ሰብስቦ ማቃጠሉ አስገራሚ የማይሆነውም ለዚሁ ነው።በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ከ25000 ቅጂዎች በላይ የተሸጠው ቀጣይ የአቤ ስራ መልካም ሰይፈ ነበልባል (1963) ህገ መንግስታዊ የዘውድ ስርአትን ማበረታታቱ አሁንም ለፍጹማዊው የሀይለስላሴ የዘውድ ስርአት ሌላ ንክሻ ነበር።የመጨረሻ ታዋቂ ስራው የ1960ና 1970 ማርክሲዝም አቀንቃኞችን የሚተችበት ፖለቲካና ፖለቲከኞች የተሰኘ ተውኔት ነበር፤ የሀይለስላሴን ስርአት በጣሉት ግራ ዘመሞች ዘንድም ይሄ ተውኔት አስጠምዶት ነበር።ድራማዎችን የሚጽፈው ተስፋዬ ገሰሰ ያረጀውን ልማዳዊ የኢትዮጲያ ትያትር ከ1960ዎቹ ጀምሮ ዘመናዊ መልክ ለማስያዝ ሞክሯል።ይህንንም በሚጽፋቸው ተውኔቶች፥ በትወና፥በአዘገጃጀት እና በማስተማር ተግባራዊ ለማድረግ ሞክሯል።አንዳንድ የመድረክ ተውኔቶቹ ጸረ-ደርግና ጸረ-አብዮታዊ ተብለው በመፈረጃቸው፥ ከሀገር ፍቅር ስራ አስኪያጅነቱ ተነስቶበወታደራዊው ጁንታ እስር ቤቶች እንዲከርም ተደርጓል።— AFRICA IN FOCUS|ETHIOPIA | PAULOS MILKIAS|2011 | PAGES305-307

## የአማርኛ (አለማዊ) ስነ ጽሁፍ አጭር ታሪክ — ክፍል ሶስት

ሎሬት ጸጋዬ ገብረመድህን ያለጥርጥር የሀገሪቱ ቁንጮ ጸሀፊ ተውኔት ነው።በዋነኝነት በአማርኛ ቢጽፍም፥ በእንግሊዝኛ የደረሳቸው ስራዎችም አሉ።በባእድ አፍ ከተጻፉት Oda Oka Oracle ይገኝበታል።ይህ ተውኔት በአለም ዙሪያ ባሉ ትያትር ቤቶች የታየ ሲሆን፥አሁንም ቢሆን በመላ አሜሪካ በሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች የጥቁር ጥናት ክፍል ከሚነበቡ መጽሀፍት ዝርዝር ውስጥ ይገኝበታል።ሌላው በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተዘጋጀው የደራሲው ተውኔት Tewodros የናፒየር ወራሪ ሀይል የ1968 ጥቃት ያስከተለውን የዳግማዊ ቴዎድሮስ እራስን ማጥፋት ይዳስሳል።ይህ ተውኔት የለንደኑን Arts Theatre ጨምሮ ብዙ ቦታ ቀርቧል።የ1966ቱን አብዮት አስመልክቶም እናት አለም ጠኑንና ሀሁ በስድስት ወርን ጽፏል።የነዚህ ተከታይ የሆነውንና ዘገየት ብሎ በ1987 የወጣውን ሀሁ ወይም ፐፑ የኢትዮጲያ መንግስት አግዶታል።የጸጋዬን ስም ለሁልግዜውም እንዲታወስ የሚያደርገው የከርሞው ሰው፥ለመድረክ በበቃ ማግስት ሀገር አቀፍ ተወዳጅነትን አትርፏል።ባባቱ ኦሮሞ በእናቱ አማራ የሆነው ጸጋዬ፥የባህላዊውንም ዘመናዊውንም ትምህርት በመቅሰሙ፥ ግእዝም እንግሊዝኛም ተምሯል።ብዙ ቋንቋዎችን አበጥሮ ከመረዳቱም በላይ፥ በልዩ ቅንብር ይጠቀማቸው ነበር።የአጻጻፍ ዘዴው ጥንካሬን የተላበሰና የስሜትን ትኩረት የሚስብ ነበር።ታሪኮቹ ብዙውን ግዜ አሳዛኝ ሲሆኑ ገጸባህሪዎቹ የኢትዮጲያውያን መራር የህይወት ትግልና ክፉ እጣ ወኪል ናቸው።ደራሲው በ1966፥ በስነጽሁፍ ዘርፍ የቀዳማዊ ሀይለስላሴ የሽልማት ድርጅት በእድሜው ከሁሉም ወጣቱ ተሸላሚ ለመሆን በቅቷል።በኩላሊት ህመም፥ በኒው ዮርክ ከተማ ከማረፉ ስድስት አመት አስቀድሞ በ1993 በስነ ጽሁፍ ለኖቤል ሽልማት ታጭቶ ነበር።ጥንታዊው የግዕዝ ይትበህልን ከዘመናዊ አጻጻፍ እኩል የተካነው ገጣሚ እና ጸሀፊ ተውኔት መንግስቱ ለማ፥ ኮሜዲን ማህበራዊ ህጸጾችን ለመንቀፍ በመጠቀም ይታወቃል።በስራዎቹ ውስጥ በዛ ብለው የሚታዩት ተምሳሌታዊና አጣቃሽ ትርክቶች ገብረገባዊ እውነትን ለማስተላለፍ ያለሙ ናቸው።የማሕበራዊ ስርአቱን አሰራር ለማስረዳት ከአንድ >>

ከሀገር ውጭ ደርሰው ሲመለሱ፥ የባህል ግጭትና የማንነት ቀውስ ውስጥ ስለሚገቡ ኢትዮጲያውያን የሚዳስሰው ባለካባና ባለዳባም በስፋት ተነባል።ጠያቂ ተብሎ የተተረጎመው የJohn B. Priestley “An Inspector Calls” ካፒታሊዝም ፊውዳሊዝም እና የመደብ ልዩነቶችን ይመረምራል።በ1974 የታተመው የልብወለድ ድርሰት ጸረ ኮሎኒያሊስት፥ የኢትዮጲያ አርበኞች በፋሺስት ኢጣሊያ ላይ የተቀዳጁትን ድል እንዲሁም በሀገሪቱ ላይ ጥሎ ያለፈውን ጠባሳ ይተርካል፤ ይሄም ድርሰት ብዙ ተከታይ አፍርቶላቸዋል።ሶስት ተውኔቶችም ተሰባስበው የተውኔት ጉባኤ(1975)በሚል ርእስ ታትመዋል።ሸሚያ(1975)የተሰኘ ሌላው የመንግስቱ ተውኔት የቢሮክራቲክ ቡርዣው መደብ የእርስ በእርስ ፋክክርና ምግባረቢስነት ይገልጻል፤የአለም ንጉስ የተሰኘ ሌላም ተውኔት ጽፏል።ብዙ ስራዎችንም ወደአማርኛ ተርጉሟል።ለአብነት ያህልም የቼኮቭ The Bear(ዳንዴው ጨቡዴ)የቶፊቅ አል ሀኪም Lust To Kill(ግደይ ግደይ አለኝ)ይጠቀሳሉ።የአባቶች ጨዋታ(1953)የኢትዮጲያን ባህላዊ ትውፊቶች በግጥም የተቀኘበት ሌላው ተጠቃሽ ልብወለድ ነው።መንግስቱ ለደራስያን የሚጠቅሙ ረጂ መጽሀፍትንም ጽፏል—የትያትር ድርሰት የአጻጻፍ ብልሀት ጥሩ ምሳሌ ነው።ደራሲው ካረፈ በኋላ በ1988 የታተመውን የአባቱን ትዝታዎችንና የራሱን ግለ ታሪክም ትቶልን አልፏል።ሌላው ታዋቂ ደራሲ፥ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለብዙ አመታት መምህር የነበረው ዳኛቸው ወርቁ ነው።ደራሲው የአማርኛ ቋንቋን የማበልጸግ ከፍተኛ ፍላጎት ነበረው።ከዋና ዋና ስራዎቹ መሀከል የአማርኛ ፈሊጦች(1978)፥ የጽሁፍ ጥበብ መማሪያ፥ የአማርኛ የጂኦግራፊ መዝገበ ቃላት(1978)እና የገለጻና የምልልስ ፋይዳ በአደፍርስ የመጀመሪያ ምዕራፍ ተጠቃሽ ናቸው።የታተሙ ልብወለድ መጽሀፎቹም ሰቀቀንሽ እሳት(1948)፥አደፍርስ(1962)፥እምቧ በሉ ሰዎች(1967)፥ ትበልጭ(1958)እና ሰው አለ ብዬ(1960)ናቸው።ዳኛቸው ማህበረሰቡን የሚያስተነትንበት እይታ ሁሌም ፍልስፍናዊ አንጻሮች አሉት።ብርሀኑ ዘርይሁን የተበዘበዙና የተጨቆኑ የማህበረሰብ አባላትን በተለይም ሴቶችን በስተኋላም ገበሬዎቹን የልቦለዶቹ አበይት ጉዳይ አድርጎ ጽፏል።በሶስት ልቦለዶቹ የሴቶች ብዝበዛ የታሪኩ ማእከላዊ አንጓ ነው—ሁለት የእንባ ደብዳቤዎች(1952) ያለርህራሄ ከተበዘበዘች በኋላ አሰቃቂ የሞት ጽዋ ስለምትጎነጭ አንዲት ሴት ይተርካል፤ የበደል ፍጻሜ(1957) እና አማኑኤል ደርሶ መልስ (1957)በዚሁ ጽንፍ ያሉ ሌሎች ልብወለዶች ናቸው።ሌላው ቀደምት የብርሀኑ ልብወለድ ድል ከሞት በኋላ(1955)የደቡብ አፍሪካ ጥቁሮች በአፓርታይድ ላይ ድል ሲቀዳጁ የሚያሳይ ትንቢት ነበር።ብርሀኑ ልዩ ክነቱ የሆነውን ታሪካዊ ልብወለዶችንም በብዛት ጽፏል—የቴዎድሮስ እንባ(1958)የንጉሱ ታሪክ በሀገራችን የታሪክ ጸሀፍት ተቀብቶ ከቆየው ጥላሸት አጽድቶ የጠራ ምስሉን ማሳየት አስችሏል።ጨረቃ ስትወጣም በዛው አመት ታትሟል።የአጫጭር ታሪኮች ስብስብ የሆነው ብር አምባር ሰበረልዎ፥ ኢትዮጲያዊ የጋብቻ ልማዶችን ይዳስሳል።ሌላው ታሪካዊ ልብወለድ ማዕበል(1958)በ1966ቱ የኢትዮጲያ አብዮትና ቀድሞት በመጣው ረሀብ ላይ የተመሰረተ ነው።ደራሲው ሶስት ተውኔቶችንም ጽፏል—ሞረሽ(1972)፥ ጣጠኛው ተዋናይ(1975)እና ባልቻ አባ ነፍሶ(1975)። የመጨረሻው ተውኔት የአድዋ ድል አርበኛ የነበሩትን የደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶን ጀግንነት ያወድሳል።የብርሀኑ የመጨረሻ የልብወለድ ስራ በ1979 የታተመው የታንጉት ሚስጥር ነው። —AFRICA IN FOCUS|ETHIOPIA | PAULOS MILKIAS | 2011 | PAGES 307-308

## የአማርኛ (አለማዊ) ስነ ጽሁፍ አጭር ታሪክ — ክፍል አራት

በአሉ ግርማ ደፋር ብእሩን የደርግ ስርአትን ፖለቲካዊ ህጸጾች ለመንቀስ በሚገባ የተጠቀመ ደራሲ ነው።የበኩር ልብወለድ ድርሰቱ የሆነው ከአድማስ ባሻገር (1962) እረፍት አጥቶ ለውጥ የሚፈልገውን ተራማጅ ወጣት ማህበራዊ ንቃተ ህሊና በአንድ ደረጃ ከፍ ያደረገ ስራ ነው።የሕሊና ደወል (1967)የሚገጥሙትን እንቅፋቶች ተቋቁሞ ስራ ለማግኘት ጥረት ስለሚያደርግ አንድ ተማሪ ህይወት የሚተርክ ነው።በመጽሀፉም በአሉ የጉልበት ስራን ያበረታታል።ይኸው መጽሀፍ ቅጹ ጨምሮ ሀዲስ (1976)በሚል ርእስ እንደገና ታትሟል።ደራሲው የተሰኘው የ1972 ሌላው የደራሲው ልብወለድ የኢትዮጲያን ማርክሳዊ አብዮት ያወድሳል።ሌሎች ሁለት ልብወለዶቹ በሀገሪቱ የነበሩትን የእርስ በእርስ ጦርነት ይዳስሳሉ—የቀይ ኮከብ ጥሪ (1972) እና በጣም ታዋቂው ኦሮማይ (1974) ። በተለይ በኦሮማይ ላይ በብቸኝነት ካሞገሰው መንግስቱ ሐይለማርያም በስተቀር ሌሎች የደርግ ባለስልጣኖች ላይ ለመቀለድ ይሞክራል።ይኸው መጽሀፍም የበአሉ መጨረሻና መውደቂያው ሆነ፤ ምክንያቱም ወዲያውኑ ዱካው ጠፋ።ከዚያን ግዜ ጀምሮም እስከአሁን ድረስ በአሉን አይቻለሁ፥ ያለበትንም አውቃለሁ የሚል

ጠፋ።አሁን ሁሉም : የሚስማማው፥

የቀለደባቸው የደርግ ባለስልጣኖች በሚስጥር አድመው እንዳስገደሉትና እስከዛሬም ድረስ ተለይቶ ባልታወቀ መቃብር እንደቀበሩት ነው። (ነፍስ ይማር) የከሸፈውን የ1953 መፈንቅለ መንግስት ተከትሎ ብዙ የልብወለድ ደራሲዎች በሀገሪቱ ብቅ፥ ብቅ ብለው ነበር፦ይህ ነው የሚባል ስራ ይዘው አልቀረቡም እንጂ።ማነው ኢትዮጲያዊው የተሰኘውን ሙዚቃዊ ተውኔት የደረሰው ታደለ ገብረህይወት፥ ዘመናዊ ስነ ግጥም ላይ አዳዲስ ስልቶችን የሞከረውና ጎን ለጎን አጫጭር ልብወለዶችን የጻፈው አበራ ለማ፥ ጣምራ ጦርን የደረሰው ገበየሁ አየለ እና ጥቂት ግጥሞችን የጻፈው ደበበ ሰይፉ ግን ሊጠቀሱ ይገባቸዋል።ሳህለስላሴ ብርሀነማርያምና ዳኛቸው ወርቁን የመሳሰሉ ደራሲዎች ከሀገሪቱ የሳንሱር መቀስ ለማምለጥ የሚጽፉበትን ቋንቋ ወደ እንግሊዝኛ ለውጠው ነበር። የ66ቱን አብዮት ተከትሎ የአማርኛ የስነጽሁፍ መጽሀፍት በብዛት ይወጡ ነበር።ይሄም የደርግን ከባድ ሳንሱር የሚያሳፍር ብርቱ ጥረት ነበር።የህዝብ መገናኛ ብዙሀን በመንግስት ቁጥጥር ስር ውለው ለፕሮፓጋንዳና ለተራማጅ አስተሳሰቦች ማስተላለፊያነት ብቻ በመዋላቸው እና የመዝናኛ አማራጮች በመጥፋታቸው፥ በሺ የሚቆጠሩ ወጣት አንባብያን ከየጥጉ የሚፈልቁትን የትየለሌ ልብወለዶች በማንበብ ተጠመዱ። መጽሀፍቱም በጣም በረከሰ ዋጋ ለገበያ በመቅረባቸው፥ ማንም ተራ ሰው በቀላሉ እንዲገዛቸው አስችሏል። አብዛኛው የአማርኛ ስነጽሁፍ ለሕብረተሰቡ የተሻለ ህይወት ለማምጣት ከሚል እሳቤ አንጻር፥ የብዙሀን ተጠቃሚነት (utilitarianism) እና ህሊናዊ መነቃቃት (conscientizati on) ላይ ቢያተኩሩም፥ ለየት ያለ ጉዳይ ይዘው የሚቀርቡም አልጠፉም።ለምሳሌ ይልማ ሐብተየስ የወንጀል ክትትል ታሪኮችን መጻፍ ላይ ያተኩር ነበር።እንደ ማሞ ውድነህ ያሉ ሌሎች ደራሲዎች ደግሞ በአማርኛ ስነጽሁፍ አንባብያን ዘንድ ተወዳጅነት እያተረፉ የመጡላቸውን የስለላ ታሪኮች ከምእራባውያን መጽሀፍት እየተረጎሙ ያቀርቡ ነበር። አማርኛ በትምህርት ቤቶች ውስጥ እንደ ማስተማሪያ ቋንቋነት በማገልገሉ፥ የመማሪያ መጽሀፍትም በዛው በመጻፋቸው፥ ማንም መደበኛ የከተማ ነዋሪ የአማርኛ መጽሀፍትን በቀላሉ እንዲያገኝ ቻለ።ከ1950ዎቹ ጀምሮም ደረጃቸውን የጠበቁ የግዕዝና የአማርኛ መዝገበ ቃላት በብዛት ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ።ከነዚህ መሀከልም የኪዳነወልድ ክፍሌ መጽሀፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ዋነኛ ተጠቃሽ ነው።ሌሎች ሁለት ትላልቅ መዝገበቃላትም የደስታ ተክለወልድ የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1962)እና የWolf Leslau English-Amharic Context Dictionary (1970) ናቸው። በመጠን አነስተኛ ለአጠቃቀም ግን የተመቸ ሌላ መዝገበ ቃላት የባሕሩ ዘርጋው፥ ዘርጋው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ነው። የአማርኛ ስነጽሁፍ በትውፊታዊ አፈታሪኮችና በምሳሌያዊ አነጋገር መስኮችም እየበለጸገ መጥቷል።በዚህም መስክ ተጠቃሽ ከሆኑት መሀከል የአባቶች ቅርስን በ1938፥ የኢትዮጲያ ባሕል ጥናት ከቡልጋን በ1960፥ ባሕላችንን እንወቅበት በ1961 እንዲሁም ስም ከመቃብር በላይን በ1956 የጻፉት ባላምባራስ ማሕተመስላሴ ወልደመስቀል ዋነኛው ናቸው። ማሕተመስላሴ ከዚህ በተጨማሪ በሌሎች የስነ ጽሁፍ ዘርፎችም ብዙ መጽሀፍትን ጽፈዋል።ከነዚህም መሀከል ስለ ኢትዮጲያ የመሬት ስሪት አስተዳደርና ግብር ጠቅላላ አስተያየት፥ እጹብ ድንቅ (1943) የተሰኘ ልብወለድ፥አማርኛ ቅኔ (1947)፥ የግብርና ጥበብ አንደኛ መጽሀፍ፥ ሰዋሰው ሰማይ (1961)፥አማርኛ ቅኔ ከነመፍቻው (1952)፥ እንቅልፍ ለምኔ (1952)፥የኛም አሉን እንወቃቸው (1957)፥ሕልቁ ትውልድ ዘንጉስ ሀይለስላሴ (1965) ይገኙበታል። ማሕተመስላሴ፥ ከነዚህ ስራዎች ሁሉ በተጨማሪ ከምኒልክ ጀምሮ እስከ ሀይለስላሴ ድረስ ያሉትን የቤተመንግስት ሰነዶች ጠቅለል አድርገው የሚዘክሩበትን ዝክረ ነገር የተሰኘ ባለ 980 ገጽ ትልቅ መጽሀፍም ጽፈዋል። —AFRICA IN FOCUS|ETHIOPIA | PAULOS MILKIAS | 2011 | PAGES 308-310

አመሰግናለሁ !

# ቤተወለድ

የደሀ ገፅሽን በስላቅ ሊገልጡ
ሀገሬ ከብርሽ ባንኮችሽ በለጡ
የባንኮችሽ ቁጥር ከገንዘብሽ ናረ
የአምናው አበዳሪ ዛሬ ተበደረ

* * *

የፎቅ አብቃይ ልጅሽን ግንባር እያወዙ
“ስራቸው” ሳይታይ ቅርንጫፎች በዙ

ለነገሩ ተይው
ድከም ሲለኝ እንጂ በከንቱ ‘ምለፋው
ነብይ ሲበዛ ነው በረከት የጠፋው
ልክ እንደ ይሁዳ
የዘመንሽ ነብያት ለየት ሚያደርጋቸው
አምላክሽን ሽጠው መሬት መግዛታቸው
ለመጎናፀፊያው ቁጥር ቢሰጣቸው
በቅዱሱ መጽሐፍ ካሉት መብለጣቸው

* * *

እና ምን ልልሽ ነው
ባለ ባንክ ልጆችሽ
ከሌለው ሰብስበው ላለው ሲያበድሩ
ሰጪና ተቀባይ
ባለ ሁለት ትርጉም ቅኔ ሆነው አደሩ

* * *

ቅኔያዊ ባንኮችሽ ባይላሉም ባይጠብቁም
ተዘርፈው ተዘርፈው ተዘርፈው አያልቁም
ለባንኮችሽ ቅኔ
ለቅኔው ህብረቃል ዜማ ወጣላቸው
“ ቆጥቡ ይሸለሙ “ ይላል ዘፈናቸው

* * *

ተበዳሪ ወስዶ
ቅንጦቱን ሲገዛ ቅንጦቱን ሲያዋዛ
ለቀለጠው ብሩ
ፍሪጅ ይሸለማል ቆጣቢ እንደዋዛ
የዋህ ቆጣቢዮች
የህብረ ቃሉን ትርጉም ሊፈቱ ቢመኙም
ሰማቸውን እንጂ ወርቁን አላገኙም

═ ‖ ═

# 400ሺ በላይ ሰዎችን ያድርሱ

ምርት እና አገልግሎቶን
በ ኑ እናንብብ ዲጅታል መጽሄት ላይ
ያስተዋውቁ !

**ይደውሉ !**

**+251 970514616**
**+251 901062515**




አዲስ ሃሳብን ለዓለም ለማስተዋወቅ (For the sake of knowledge's) የሚደረግ ጥናት (Basic or Pure Research) እንዲሁም ነባራዊ ሁኔታዎች የፈጠሩትን ችግር በማሳየት መፍትሄ አፈላላጊ ጥናት (Applied Research) ለማድረግ፤ ማንኛውንም የተፈጥሮ ሳይንስም ሆነ የማህበራዊ ሳይንስ (PhD, MSc, MA, BSc, እና BA) አጥኚዎች የሚከተሏቸው ስልቶች የሚከተሉት ብቻ ናቸው.....

1. Experimental:- ሙሉ ለሙሉ መለኪያዎችን (Explanatory/Independent variables) በቁጥጥር ስር አድርገን ስናጠና ማለት ሲሆን፤ #ለምሳሌ ሁለት ተመሳሳይ ዝርያ፤ ቀለም፤ ጾታ እና እድሜ ያላቸው አይጦችን ተመሳሳይ ምግብ እና ውሃ እየሰጡ፤በተመሳሳይ እቃ ውስጥ በማስቀመጥ ለአንዷ A የሚባል መድሃኒት ለሌላኛዋ B የሚባል ሌላ መድሃኒት ቢሰጣቸው እና A የሚባለውን መድሃኒት የወሰደችው አይጥ ብትሞት ለመሞቷ ምክንያት መድሃኒቱ እንደሆነ እርግጠኛ ነን ማለት ነው ምክንያቱም ከውጫዊ ተጽኖ እንዲጠበቁ ተደርጎ ስለነበር ማለት ነው፤Naturalscience፤ Health Science እና Engineering ለዚህ አይነቱ ጥናት አመቺ ናቸው፡፡ #ማሳሰቢያ በሰዎች ላይ ወይም በSocial Science(ኢኮኖሚክስን ጨምሮ) ትምህርት ዘርፍ የዚህ አይነቱ የጥናት ዘዴ ፍጹም የማይቻል ነው!!

2.Quasi-experimental:-በተወሰነመልኩመለኪያዎችን (Explanatory/Independent variables) በቁጥጥር ስር አድርገን ስናጠና ማለት ሲሆን፤ #ለምሳሌ ሁለት በጾታ የተለያዩ፤ ተመሳሳይ ዝርያ፤ ቀለም እና እድሜ ያላቸው አይጦችን የተለያየ ምግብ እና ውሃ እየሰጡ፤ በተመሳሳይ እቃ ውስጥ በማስቀመጥ ለአንዷ A የሚባል መድሃኒት ለሌላኛዋ B የሚባል ሌላ መድሃኒት ቢሰጣቸው እና A የሚባለውን መድሃኒት የወሰደችው አይጥ ብትሞት ለመሞቷ ምክንያት በጾታዋ ልዩነት፤ በመድሃኒቱ ወይም በምግቡ መሆኑን በእርግጠኛነት ለመናገር አይቻልም ምክንያቱም ከመድሃኒቱ ውጪ ሌሎች ተጽኖዎች ስላሉ ማለት ነው፡፡ የSocial Science ትምህርት ዘርፍ በዚህ አይነቱ የጥናት ዘዴመካሄድ ይችላል፡፡

3. Non experimental:- ከExperimental የጥናት አይነት ፍጹም በተቃራኒው ሁሉም(Explanatory/Independent variables) ውጫዊ ተጽኖ ኖሮበት ሲካሄድ ማለት ነው፤ የBehavioral Science ጥናቶችን ማንሳት ይቻላል፤ #ለምሳሌ ስለ ሰዎች ባህሪ ለማጥናት ቢታሰብ ባህሪ በተለያዩ ምክንያቶች ተለዋዋጭ ስለሚሆን (Explanatory/Independent variables)ን ተቆጣጥረን ስለማንይዛቸው በውጤቱ እርግጠኛ መሆን ያስቸግራል፡፡#Descriptive (ገላጭ የአቀራረብ ዘዴ መጠቀም)፤ Causal (ምክንያት እና ውጤትን አመላካች ጥናት)፤ Meta analysis (የሌሎች የጥናት ውጤቶችን በማሰባሰብ ንጽጽር ማከናወን)፤ ወዘተ ከላይ የተዘረዘሩትን የጥናት ስልቶች ማቅረቢያ ዘዴዎች መሆናቸው መታወቅ አለበት!


**The Ethiopian Economist View**
ቴሌግራም
እዚህ ይጫኑ

# ኢትዮጵያዊነት ረቂቅ ነው!

ከሽናፌ ጌታቸው

ለገሀር ድሮ ድሮ መዲናችን አዲስ አበባ ሳትወፍር እና እንዳሁኑ ቦርጫም ሳትሆን በፊት ነው አሉ የከተማዋ እንብርት ለገሃር( አንዳንድ ጽሁፎች ለገሀሬ ይሉታል) አካባቢ ነበር አናም ሰዎች ለስራም ለንግዱም ሆነ ከመዲናችን አዲስ አበባ ወደ ድሬደዋ፤ ሀረር ፤እና ጅቡቲ ለመጓዝ ሲያስብ የሚመጡባት የከተማዋ መካከለኛ ስፍራ ነበረች ፡፡ በህንጻዎች መደራረብ ግርማ ሞገሱ ያልደበዘዘው የለገሀር ባቡር ጣቢያ አሁንም ድረስ በኩራት ቆሞ ይታያል፡፡ መቼስ በሀገራችን ካሉት የመንግስትም ሆነ የግል መካነ-አእምሮ(ዩኒቨርሲቲ) ጎራ ብሎ ተምሮ ቆብ የደፋም ይሁን ገና በለጋ እድሜው ከቀለም ትምህርት የተቆራረጠ ስራ ፈላጊ ሁሉ ይህችን ቦታ የሚያስታውሳት በባቡር ጣቢያዋ ሳይሆን በ የስራ ማስታወቂያ ማስነበቢያ ቦታዋ ነው፡፡(እኔም አንድ ሰሞን ጽኑ ደንበኛዋ ነበርኩ )ስልጣኔ ናፋቂው የ ሀገሬ ውድ መሪ በሆኑት እምዬ ሚኒሊክ በተሰራው በዚህ የባቡር መዳረሻ ፊት ለፊት አንድ ታላቅ የመታሰቢያ ሀውልት በሞገስ ተሰይሞ ይታያል ፤ የሞህ አንበሳ ዘ-እምነተ ነገድ ይሁዳ አርማ የተቀረጸበት የመታሰቢያ ሀውልት ይህ መታሰቢያ ሀውልት በሀገረ ፈረንሳይ ተቀርጾ በሺ ዘጠኝ መቶ ሃያ ሁለት ህዳር 24 ቀን በክብር ቆመ ፡፡ በ1935 ወራሪ ጣሊያን ኢትዮጲያን በወረረች ሰአትም ሀውልቱ በጣሊያን የጦርመሪዎች ተሰርቆ በጣሊያን ሮም በሚገኝ አንድ ፓርክ ውስጥ ቆመ፡፡ዛሬ በጽሁፌ ላነሳውና ታሪኩን ልዘክርለት የወደድኩት ኢትዮጲያዊነትን አጉልቶ ላሳየኝ ትውልደ ኤርትራዊው ስለ ጀግናው ዘርአይ ደረስ ነው ፡፡ከዕለታት በአንዱ የጣሊያን አመታዊ በዓላቸው ቀን ፡ ጀግናው ዘርዓይ ደረስን ከአሥመራ በጣሊያን ቋንቋ አስተርጓሚነት ወስደውት እዚያው ስለነበር፡ የሃገሩን የአርበኝነት ዩኒፎርም እስከነ ሙሉ ትጥቁ ጎራዴውን ጨምሮ ለብሶ በዓሉ ቦታ ላይ እንዲገኝ አደረጉ። ከዚያም የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማን መሬት ላይ አንጥፈው እየረገጡና ምራቃቸውን እየተፉ ሲረማመዱበት ጀግናው ወጣቱ ዘርዓይ ደረስ መታገስ አልቻለም፤ አጠገቡ ካሉት በመጀመር የጣሊያን ወታደሮች አንገት መቀንጠስ ጀመረ፤ጣሊያኖች እግሬ አውጪኝ ሸሸት ጀመሩ፡ ዘርዓይ ደረስን የሚያስቆመው የሰው ክንድ እንዳልሆነ አወቁ፡ ወዲያው ተኩሰው እግሩን አቆሰሉት። ወደ እስር ቤት አስገብተውት ቢሆንም ጀግንነቱ በመላው ጣሊያን ሃገር ገነነ። ሆስፒታል አስገብተው በሕክምና ሂደት ላይ ሳለ፡ ኢትዮጵያ ሃገራችን ድል እንደተቀዳጀች፡ ሙሶሊኒ በገዛ ሕዝቡ ተገድሎ አዲስ የጣሊያን መንግሥት ስለተመሠረተ፡ ግርማዊ ጃንሆይ አጼ ኃይለሥላሤ፡ በምርኮና በግዞት ጣሊያን የወሰዳቸውን አርበኞች ሲያስመልሱ፡ጣሊያኖች ሆን ብለው ይህንን ወጣት ጀግና ገድለው ታሞ ሞተ በማለት ሕይወቱን ቀጥፈውት እንደነበር የኢትዮጵያ ታሪክ ያወሳሉ፡፡





## ABYSSINIAN SHOT IN ROME

### AN INTERRUPTED PRAYER

FROM OUR OWN CORRESPONDENT

ROME, JUNE 15

Romans hurrying to lunch to-day saw a negro, presumably an Abyssinian, praying before the large gilt Lion of Judah, which was taken from the Imperial Palace in Addis Ababa and now reposes at the foot of the monument in honour of the 500 Italians who were killed at the battle of Dogali in the Italo-Abyssinian war in 1897.

A crowd gathered, and when an army officer attempted to prevent the negro from continuing his devotions, the latter produced a scimitar from his clothing and slashed at him, inflicting a serious wound. A butcher's boy who intervened was also slashed, whereupon two soldiers fired four revolver shots at the negro and put him out of action, but not before he had wounded the soldiers.

የዘርዓይ ድረስን ድንገተኛ አሟሟት እና መጨርሻ በተመለከተ ጥላሁን ብርሀነ ስላሴ የተባሉ ፀሃፊ “የ 20ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ” ባሉት መፅሃፋቸው እንዲህ ይላሉ፤”ዘርዓይ ድረስ የፈጠረው ሁኔታ ጣሊያኖችን ስላስቆጣቸው፣በንዴት ጣሊያን ሀገር ከነበሩት እስረኞች 147 ያህሉን ወደ አዚናራ የእስር ደሴት ሲወስዱ፤ ሌሎችን ደግሞ ሰብስበው ወደ ሞቃዲሾ አመጧቸው፡፡ ከነፃነት በኋላ ዘርዓይ ድረስ ወደ ሀገሩ ኢትዮጵያ እንዲመለስ ተወስኖ ሊመጣ ሲል ክትባት ነው ብለው በመርፌ በሰጡት መርዝ አድርገው ገደሉት”በሁላም ለስሙ ማስታወሻ የመጀመርያዋ የኢትዮጵያ የጦር መርከብ ዘርዓይ ድረስ ተብላ ተሰይማለች። ዘርዓይ ድረስ ከሞቱ ከብዙ ዓመታት በሁላ ይልማ ሙናዬ የተባሉ ደራሲ “ ዘርዓይ ድረስ” የሚል ታሪካዊ ተውኔት በመፃፍ ለመድረክ እና ለንባብ በማቅረባቸው በወጣቱ ትወልድ ዘንድ የዘርዓይ ድረስ ታሪክ እንዲታወቅ አድርገዋል ፡፡ለዚህ ነው ኢትዮጲያዊነት ረቂቅ ነው ሚባለው !እናም ከ ኤፍሬም ስዩም የአንድ አፈር አፈሮች ግጥም ላይ ጥቂት ስንኝ በመዋስ ላብቃ

እንደ ማህተብ የእምነት ክር ፍቅር ድሩ ላይበጠስ
እኔና አንተኮ የአንድ እናት ልጆች
ወንድም እና እህቶች
ያንድ አፈር አፈሮች

እርስት አፈሩማ ይቅርም ከወደዚ ይሂድም ወደዚያ
ያው ነው የኢትዬጲያ ያንድ አፈር መጠሪያ

ወዲያ ካለው የቀድሞዋ
ወዲህ ካለው የእስካሁኑዋ

ምንጭዎች ፡-የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል መታሰቢያ ገጽ እነዲሁም በ www.sewasew.com ላይ ዘርአይ ደረስ ማን ነው በሚልየቀረበ ጽሁፍ፡፡

በካዩ በቀለ ወያ

# አንድ ቀን ስንት ነው?




እኛ አይደለን እንዴ...
ከነፍሳችን በራፍ ፣
ዘጠኝ ሞት ቆሞ ፣ የሚጠባበቀን
ላንዱ በር ስንከፍት ፣ ስምንት ሞት የሚያንቀን
እኛ አይደለንም ወይ?
"ለበጎ ነው " እያልን ፣
እድሜያችንን ያጣን ፣ ስንጠብቅ አንድ ቀን ።
::::::::::::::::::::::::::::

ለመንጋት አንድ ቀን
ለመድረስ አንድ ቀን
ለማግኘት አንድ ቀን
አንድ ቀን
አንድ ቀን
አንድ ቀን
አንድ ቀን
"አንድ ቀን" እያልን...
ተስፋችንን ሁሉ ፣ አንድ ቀን ላይ ጥለን
አንድም ቀን ሳይሞላ ፣ ዘመን የጎደለን
እኛ አይደለንም ወይ?
ሁሉን የምንጠብቅ ፣
ሁሉንም የምናልፍ ፣ "ለበጎ ነው" ብለን፡፡
::::

ለበጎ ነው እያልን
የምናልፈው ክፋት ፣ ጥሩ ቀን ባይሰጥም
ፍቅርም ህግ አለው !
ትእግስትም ልክ አለው
በጥላቻ እስኪረክስ፣ አይለማመጥም
ብርሀን የሚነግድ
ሻማ ለመግዛት ሲል ፣ ፀሐዩን አይሸጥም!!!
:::::

መደምደሚያ!!!
አንድ ቀን ፍለጋ ፣ አንድ ዘመን ጥሎ
አይሆኑትን ሆኖ ፣ አይችሉትን ችሎ
ማለፍ በጎ አይደለም! ፣ "ለበጎ ነው" ብሎ!!!

መ/ር ከበባው ከሰቱ

# ይድረስ ለእግዚአብሔር ልጆች
## (A Message to the children of God)

ይህ መጽሐፍ ለማን ተፃፈ?

I am against religion because it teaches us to be satisfied with not understanding the world. —Richard Dawkins

ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በዋናነት ለአማኞች ነው፡፡ በተጨማሪም ኢ-አማኞች፣ ያልወሰኑ ሰዎች፣ ተማሪዎች እና ተመራማሪዎችም ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

1ኛ. አማኞች፡-መጽሃፉ ለሁሉም አማኞች የተዘጋጀ ቢሆንም በተለይ ግን ቀጥሎ ለተዘረዘሩት እንዲደርስ እፈልጋለሁ።

1.ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ፣ ለካቶሊክ፣ ለፕሮቴስታንትና ለሙስሊም ሊቃውንት

2.ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ አጥማቂዎች እና ለፕሮቴስታንት ነብያት፣ ሀዋርያትና ቴሌቫንጋሊስቶች

3.ለዲ/ን ዳንኤል ክብረት፣ መ/ር ዘበነ ለማ፣ ለመ/ር ሮዳስና ለመጋቤ ሃዲስ እሸቱ አለማየሁ

4.ለንቡረ ዕድ ኤርሚያስ ከበደና ለተክለ ኪዳን

5.ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ን ሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምርያ ማህበረ ቅዱሳን

6.ታሪክን በተለይ የኢትዮጵያን ታሪክ በመስኮት ተምረው ለሚሰብኩን ሙህራን

አማኞች ሆይ እንደ አማኝ ከመፅሀፉ ሀሳቦች ከአብዛኛዎቹ ጋር አትስማሙም ይሆናል ሲጀምር ስለኢ-አማኞን አመለካከቶች እንድታውቁ እንጅ እንድትስማሙ አልጠብቅም፡፡ ይህንን መጽሐፍ ማንበቡ ኢ-አማኞች ምን እንደሚያምኑ፣እንዴት እንደሚኖሩ እና ስለ ተፈጥሮ ያላቸውን ግንዛቤ ምን እንደሚመስል እንድትመለከቱ ያስችላችኃል፡፡ እነዚህ ሰዎች የእናንተን እምነቶች እንዴት እንደሚጠራጠሩ ትረዳላችሁ፡፡ ስለእምነታችሁ ለመሟገት እቅድ ካላችሁ ይህ መጽሐፍ የተቃዋሚዎች ያለማመን ምክንያቱን በመረዳት ምክንያታዊ ክርክር እንድታደርጉ ሊረዳችሁ ይችላል፡፡ ስለ አምላክ እና ስለ ሃይማኖት በጠንካራ ማስረጃዎች ላይ የተመሰረተ ፍሬያማ ውይይት ማድረግ ትችላላችሁ፡፡ የሂስ መፅሀፍ እንደመሆኑ እምነታችሁን እስከቻልኩት ድረስ ለመተቸት ሞክሬአለሁ ከጥቂት ሙገሳ ጋር፡፡ ለምን ወደ ትችቱ አደላህ ብትሉ ሀይማኖታችሁ በእየ ቀኑ ሳይወደስ አይዉልም የጎደለው ሊያስተካክል የሚችል ትችት ነው፡፡ መፅሀፉን አንባችሁ ልማርበት የሚችል የማስተባበያ ፅሁፍ እንደምትልኩልኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ወገኖቻ ብትችሉ ውደዱኝ ፍቅር ነው የራበኝ፣ ባትችሉ ግንሽህ ጊዜ ጻፉብኝ፣ አምራችሁ እርገሙኝ፣ አስደግሙብኝ፣ እንደሰይጣን ጥሉኝ፣ ስደቡኝ፣ መሳለቂያ አድርጉኝ ይህ ሁሉ ለኔ ፀጋ ነው። ነገር ግን ድንጋይ ለመወርወር፣ ቡጢ ለመሰንዘር፣ ለማሰር እና ለማሳደድ ለምታስቡበምታምኑት አምላክ፣ በምትወዷት ሀገር በተለይም በወላጅ እናታችሁ ልለምናችሁ ተውኝ። ይህን የምላችሁ ስለምፈራ ብቻ አይደለም የተለየ ሃሳብ ያላቸው ሰዎች በህዝብ ፊት ሲደበደቡ፣ ሲሰቀሉ፣ ሲዘረፉ፣ ሲታሰሩ እና ሲሳደዱ ስላየሁ ነው። እኔም ብዙ ጊዜ <ሰው የሚያስብ ፍጡር ነው> የሚለውን እስክጠራጠር ድረስ በአሳዳጆቹ ቀለበት ውስጥ ገብቸ አውቃለሁ። አንዳንዴ ስንተኛው ክፍለ ዘመን እንዳለን ግራ ይገባኛል። በአሪት ዘመን ይሆን እላለሁ። ስንተኛው ክፍለ ዘመን ላይ ነን እባካችሁ???

ብዙ እቅድ አለብኝ ብዙ መመራመር፣ ብዙ መፈላሰፍ፣ ብዙ መጎብኘት፣ ብዙ ማንበብ እና መጻፍ፣ ብዙ መማር እና ማስተማር አለብኝ። እንዴ! የአፍሪካን መዲና አዲስ አበባን፣ ውቧ ባህር ዳርን፣ ንግስቷ ጎንደርን፣ ጥንታዊቷ አክሱምን፣ ባለድሏ አድዋን፣ ድንቋ ላሊበላን፣ ሞቃቷ አፋርን፣ ጠበብቷ ሀረርን፣ ስብጥር ደቡብን፣ አርባምንጭ ሀዋሳን፣ የገዳ ስርአትን ሌሎች ሌሎችንም የማየት ህልም አለኝ። ኢትዮጵያ እኮ የሚስጢር መፅሃፍ (መጽሃፈ ሚስጢር) ናት። እንዴ! በማይክሮስኮፕ ህዋሳትን ሳላይ፣ በቴሌስኮፕ ህዋውን ሳላየው፣ በጥንት ግሪኮች የተተከለውን የእውቀት ዛፍ ፍሬን ሳልበላው ማለፍ አልፈልግም። ብዙ ያላነበብኩት መፅሃፍ፣ ያላሳትምኩት ረቂቅ ጹህፍ፣ ያላጣጣምኩት ሙዚቃ፣ ያልጎበኘሁት ቦታ፣ ማየት የሚገባይ ያላየሁት አለም አለ። ይህን ሁሉ ከምትለማማጥ ለምን አርፈህ አትቀመጥም ልትሉኝ ትችላላችሁ እኔ ግን ከአባቶቼ አልበልጥም እላችኋለሁ፣ ድግሜም ህልም ፈርቸ ሳልተኛ አላድርም እላችኋለሁ። ለማንኛውም የሰለጠነ ሰው ይግጠምህ፣ የተማረ ይግደልህ በሉኝ።

እንደ ተወዳጁ ዲ/ን ዳንኤል ክብረት የሰለጠኑት አማኞች የእኔን መሰሎችን ሃሳብ እንደ መልካም ተግዳሮት እና ግብዐት ይጠቀሙባታል። ያም ብቻ ሳይሆን አማኞች ልበ ሙሉ እንዲሆኑ ያስተምራሉ፣ ምሳሌ ይሆናሉ። ዲ/ን ዳንኤል ክብረት በዕውቀቱ ስዩም ‘እግር አልባ ባለ ክንፍ’ ብሎ ለጻፈው ‘እግር ያለው ባለ ክንፍ’ ሲል የመልስ ምት በሰጠበት የዳንኤል ክብረት ዕይታዎች ከተሰኘው ድረ ገጹ እንዲህ ያስደምመናል፡-“ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍቷን በቀኖና እንድትወስን፣ ሥርዓቷን እንድትወስን፣ የሃይማኖት መግለጫዋን ወስና እንድታወጣ፣ ሕግ እና ደንብ እንድትሠራ፣ መጻሕፍትን እንድትጽፍ፣ ያደረጓት ተግዳሮቶች በየዘመናቱ መኖራቸው ነው፡፡ ሄሊቪዲየስ ተነሥቶ በቅድስት ድንግል ማርያም ላይ የተለየ ትምህርት ባያመጣ ኖሮ አባ ጄሮም እና አባ ኤጲፋንዮስ የጻፏቸውን መጻሕፍት ባላገኘን ነበር፡፡”ይላል ምሳሌውን ይቀጥልና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ትልቅ ክብር የሚሰጣቸው አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ስላደረጉት ነገር ይነግረናል። “ቴዎድሮስ የተባለ የጦር አዛዥ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫን ስለ ሃይማኖት ባይገዳደረው ኖሮ አስደናቂውን ርቱዐ ሃይማኖት የተሰኘ መጽሐፍ ባላገኘን ነበር፡፡ የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋዕል እንደሚነግረንም በንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን በሃይማኖት ምክንያት ክርክር ሆነ፡፡ አባ ጊዮርጊስም ከአንድ ፈረንጅ ጋር ተከራክሮ ረታው፡፡ መጽሐፈ ምሥጢርንም ደረሰ።” ዲ/ን ዳንኤል ክብረት የምናምነውን የማያምኑ መኖራቸው እምነታችንን እንደሚያጠነክሩልን ሲገልፅ እንዲህ ይላል፡- “መልአከ ብርሃናት አድማሱ ጀንበሬ (የሞተ ልጃቸውን በጸሎት ያስነሱ ብርቱ አማኝም ነበሩ ይባላል) ያንን የመሰለ ኮኩሐ ሃይማኖት የተሰኘ መጽሐፍ እንዲጽፉ ምክንያት የሆናቸው አባ አየለ ተክለ ሃይማኖት የሚባል ካቶሊካዊ ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጻፈው ጽሑፍ ነው፡፡ እነ አስረስ የኔሰው ያንን የመሰለ ትቤ አኩስም መኑ አንተ የተሰኘ የታሪክ፣ የእምነት፣ የቅርስ እና የሥነ ልሳን መጽሐፍ የጻፉት በወቅቱ ለተነሡት የታሪክ፣ የቋንቋ እና የእምነት ተግዳሮቶች መልስ ለመስጠት ነው፡፡”(በቅንፋ የተጨመረውን ያገኘሁት ከካሳሁን አለሙ ተጠየቅ ድህረ ገጽ ነው)

ዲያቆን ዳንኤል ክብረት አቡነ ተክለ ሃይማኖት 'እግር አልባ ባለ ክንፍ' ሳይሆኑ 'ክንፍ ያለው ባለ እግር' መሆናቸውን ለማስረዳት ታሪክን እና እምነትን መሰረት አድርጎ አብራርቶ መልሶታል፣ በአንድ ወር ደሞወዝ የሚገዛ ዳጎስ ያለ መፅሃፍም ለአቡኑ ጽፎላቸዋል። (በነገራችን ላይ እኒህ አወዛጋቢ ቅዱስ ሰይጣንን ወንጌል ሰብከው ገርዘው ስሙን ክርስቶስ ሀረዮ በማለት ሰይመውና አመንኩሰው በዘመኑ ሁሉ መነኮሳቱን በቅንነት አገልግሎ ሲሞት መንግስተ ሰማይያት እንዳስገቡት በገድላቸው ይተርካል። ይገርማል!) ዳንኤል ወቅታው እይታወቹን በሚዳስስበት ድህረ ገጹም የበዕውቀቱን ጥርጣሬ እንደጠቀሳቸው አባቶቹ በግብዐትነት ተጠቅሞበታል።ከዳንኤል ክብረት ጋር የማያግባቡን ብዙ ልዩነቶች ቢኖሩኝም እንደሱ የማደንቀው አማኝ ፈልጌ አጥቻለሁ። እንደ ብዞዎቹ ተቆርቋሪ ነን ባዮች ማጥላላት አይታይበትም፣ ጠላቴ ከማለት ይልቅ ወንድሜ ማለትን አስቀድሟል። ብዙዎች ግን አይነኬ ሀይማኖታቸውን በዕውቀቱ ስዩም ስለነካባቸው አይናቸው ቀልቷል፣ እስከ መደባደብም የደረሱ አሉ።እነዚህ የሂትለር ርዝራዦች ለቡጣ ቡጢ እንጅ ለውይይት ስላልታደሉ ያስፈራሉ፣ ያሳፍራሉም።

የተማሩት የተመራመሩት እነዲ/ን ዳንኤል ክብረት ግን የሰጡን የመጻፍ ነጻነት ብቻ ሳይሆን በመሃይሞች ለሚደርስብን ጥቃት ጥብቅና እስከመቆም ነው። በምንም መንገድ ይላል ዲ/ን ዳንኤል ክብረት "በምንም መንገድ ይሁን በምንም እንደ በዕውቀቱ ያሉ ጸሐፍት የመጻፍ ነጻነታቸው መከበር አለበት፡፡ ጥያቄ ያለው ወይንም በሃሳባቸው የማይስማማ ሰው እስከ ሕግ አግባብ ድረስ በመሄድ ጤናማውን እና የሠለጠነውን መንገድ ተከትሎ መሞገት ይቻላል፡፡ አንድ ጸሐፊ በመጻፉ ምክንያት ብቻ አካላዊም፣ ሃሳባዊም ጥቃት እንዳይደርስበት የምንከላከለው በሚጽፈው ሃሳብ ስለምንስማማ ብቻ መሆን የለበትም፡፡ ለማንስማማበትም ሃሳብ ነጻነት መሟገት አለብን፡፡ ሃሳቡን እየተከራከርነውም፤ መብታችን ተደፍሯል ብለን በፍርድ ቤት እየከሰስነውም ቢሆን ለሃሳብ ነጻነቱ ግን መሟገት ግድ ይለናል፡፡እናም በዕወቀቱ ይጻፍ፣ የማልስማማበትንም ነገር ይጻፍ፣ እኔም የምስማማበትን እይዛለሁ፣ የማልስማማበትን እሞግታለሁ፡፡ ለበዕውቀቱ የመጻፍ ነጻነት ግን ጥብቅና እቆማሁ፡፡" (የዳንኤል ክብረት ዕይታዎች ድህረ ገጽ)

ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ይህን ተስፋ ሰጭ ፅሁፍ በመጻፉ እኔን ጨምሮ ብዙ አድናቂዎቹ ቢደሰቱም አንዳንዶቹ የዘራፍ ዘመን አስተሳሰብ አራማጆች ግን ከበዉቀቱ ይልቅ ዳንኤል ያናደዳቸው ይመስላል። እነዚህን ሰዎች ለማስደሰት ሲል ዳንኤል በዕውቀቱን መሳደብ ነበረበት፣ መናፍቅ ምናምን ማለት ነበረበት ግን አላደረገውም ይልቅስ በዕውቀቱ ሥዩም ነገሮችን በአዲስ መልክ ከሚያዩ ጥቂት የሀገራችን ጸሐፍት አንዱ ነው ሲል አወደሰው፡፡ ገና ብዙ ሥራ የሚጠበቅበት ወጣት ጸሐፊም እና ሕይወቱን ለጽሑፍ የቀየደ ሰውም ነው በማለት የቤት ስራ ሲሰጠው ይታያል። መታደል ካመኑም ከተማሩም እንዲህ ነው። ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በርታ ተበራታ እላለሁ፣ ምን አለ ያለ ስጋት በነጻነት የምንኖርበት ዘመን በሆነልን ወይም ቢያንስ ሲናገሩ እንጅ ሲናገሯቸው የማይወዱ ባይኖሩ።

በስጋቴ ዙርያ አንድ ኤቲስት የማህበራዊ ሚድያ ጓደኛየ በሚድያው ገጽ ያሰፈረውን ላካፍላችሁ እኔም እጅግ በጣም እስማማበታለሁ። "የምፅፈዉ እኔ የተሰማኝን እንጅ እናንተ የተሰማችሁን አይደለም። የተሰማችሁን ፅፌዉ ካገኛችሁ መልካም ነዉ። ካልፃፍኩትም አትበሳጩ። ምክንያቱም እኔ እናንተ አይደለሁም። ሰወች ይጠሉኛል ብየ የማምንበትን ነገር ከመፃፍ ወደ ኋላ አልልም። ሰወች እንዲወዱኝ ብየም የማላምንበትን ነገር አልፅፍም። ስለዚ እኔ እንድትወዱኝም ሆነ እንድትጠሉኝ ሆን ብየ የምፅፈዉ ነገር አይኖርም። እኔ የምፅፈዉ የራሴን ሀሳቦች ነዉ። ሀሳቦቸ ሁሌም ትክክል ሊሆኑ አይችሉም፣ የተሳሳተ ሀሳብ ልፅፍም እችላለሁ። እኔ ለእናንተ አስቤ አልፅፍም እናንተም ለኔ ብላችሁ አታነቡም። ስለዚ እኔም የተመቸኝን የመፃፍ እናንተም የተመቻችሁን አብባችሁ ያልተመቻችሁን የማለፍ መብት አላችሁ። የናንተና የኔ ግንኙነት የሻጭና የገዥ ግንኙነት ነዉ። ሻጩም እቃዉን የሚሸጠዉ ለገዡ አስቦ አይደለም። ገዡም እቃዉን የሚገዛዉ ለሻጩ አስቦ አይደለም። በመሀል ግን ሁለቱም ተጠቃሚ ይሆናሉ።"<ከማመን መጠራጠር ይሻላል>

በጣም የሚገርመኝ አይቶ ማለፍ፣ ማስተባበል፣ አለማንበብ፣ አለመግዛት፣ ዲሌት፣ አንፍሬንድ፣ ብሎክ እና የማሳሰሉት የማንፈልጋቸውን የመከልከያ መንገዶች እያሉን ይህ ሚድያ ይዘጋ፣ ያ መጽሀፍ ይቃጠል ወዘተ እያልን መንግስትን የምንወተውት አለን። ወገኖች እናንት ስለ ሌላ ሰው እያወራችሁ ስለእናንተ የሚያወራውን አትከልክሉት። ከኢ-አማኒ ወደአማኒ የሚሰነዘር ማንኛውም ሃይማኖት ነክ ጉንተላ ምክንያታዊ አይደለም የምትሉ እናንተ ስለ ኢ-አማኝ በህዝብ ሚድያ ሳይቀር ስትደነፉ ቅር አይላችሁም? ተስፋ አደርጋለሁ እናንተ የሰው ስጋ ካልበላችሁ የእናንተን ስጋ የሚበላ የለም። መውገር ያለበት ንጹህ የሆነ ብቻ ነው። ማን ነው ንጽህና እውነተኛ ማንም የለም። ቤተ ክርስቲያን በአዋጅ ደረጃ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ረቂቅ ሕገ ቤተክርስቲያን፣ አንቀጽ 3 ቁጥር 7-8 "ቤተክርስቲያን ያሏትን ጥንታውያት መጻሕፍት እየተረጎመችና እያሳተመች ለምእመናን አገልግሎት የማዋልና የማሰራጨት እንዲሁም የጥናትና የምርምር ተቋማትን የማቋቋም መብት አላት። ቤተክርስቲያን ማሠልጠኛዎችንና መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶችን የማቋቋም፤ ለተቋቋሙትም እስከ ኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ዕውቅና የመስጠት፤ በትምህርት ቤቶቿም አማካይነት ሃይማኖቷንና ቀኖናዋን የማስተማርና የማስፋፋት፤ በየገዳማቱና በየአድባራቱ የሚገኙትን ጥንታውያን የአብነት ትምህርት ቤቶች የማጠናከርና ከየትምህርት ቤቱ ለሚመረቁ መምህራንና ደቀመዛሙርት የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት መብት አላት. . ." እያለች ከኔ ውጭ ወደ ውጭ የምትል ከሆነና ልጆቿን አብሮ መኖርን እንዲላመዱና ልበ ሙሉ የማታደርግ ከሆነ እኛስ የት ሂደን ሀሳብችንን እናሰማ።

ቀና አስተሳሰብ ያላችሁ ውድ አማኞች ክህደቴን በማሰብ እኔ ስለምቃጠልበት ሲኦል አንዳች እንዳታስቡ በወላጆቸ በኩል ከ10 ትወልድ በላይ ዋስትና ተሰጥቶኛል። ከፈለጋችሁ ከእልፍ ቅዱሳን ውስጥ ለአንዱ ቅዱስ አገልጋይ ክርስቶስ የገባለትን ቃል ኪዳን አንቡ፡፡ ለነገሩ በወላጆቸም በኩል ብቻም ሳይሆን እኔ እራሴ ከበላየ ሰብ የተሻለ በብዙ ቅዱሳን ስም እመፀውታለሁ በተለይ በድንግል ማርያም ስም፣ ገዳማት እጎበኛለሁ፣ በክበረ ብአላት ቤተ ክርስቲያን እሳለማለሁ ወዘተ፡፡ይህም እንኳ ባይሆን ቅዱሳን ሲኦልን ሲበረብሩ በክንፋቸው ተጥልየ ገነት እገባለሁ። ስለዚህ ጌታ እኔን በተመለከተ ልዩ የህግ ማስተካከያ እስካላደረገ ድረስ ከእናንተ ጋር መንግስቱን እወርሳለሁ አትጠራጠሩ፡፡ ለማንኛውም የሚያደርገውን አያውቅምና ሀዋርያው ቅዱስ አርዮስን ማረው እያላችሁ አንቡት፡፡

2ኛ. ኢ-አማኞች፡-ይህ መጽሐፍ አምላክ የለሾቹ እራሳችሁን በደንብ እንድትገልጹ ይረዳችኃል፡፡

በእርግጥ ማስረጃን ማቅረብ ያለበት ፈጣሪ አለ የሚሉት ናቸው፡፡ እግዚአብሄርን በተመለከት አማኞች መኖሩን ማረጋገጥ ካልቻሉ ለእናንተ በቂ ነው፡፡ ግን ከዚህም አልፎ አለመኖሩን ማስረዳት ባይጠበቀባችሁም ለውይይት ሲባል ከመፅሀፋቸው እና ከተፈጠሮ እያመሳከራችሁ ላመናችሁበት እውነት ተጨማሪ ዘዴዎችን ማወቅ ይኖርባችኃል፡፡ የዚህን መፅሀፍ ክርክሮች በመረዳት እና ሌሎች እንዴት እንደሚረዱ በመመልከት ሎጂካዊ በሆነ መንገድ ውይይቶች እንድታደርጉ ሊያግዛችሁ ይችላል፡፡ከአማኞች ወይም ከህሊናችሁ ጋር ለመከራከር በመጀመርያ እግዚአብሄር ሊኖር ይችላል ብላችሁ ተነሱ፡፡ ቀጥሎ መመራመር ይቻላል፡፡ ሲጀመር አለ ወይም የለም ብላችሁ ከዘጋችሁት ግን መመራመር፣ መፈላሰፍ አያስፈልግም፡፡

እኔ አርዮስ በዚህ መጽሐፍ የእኔና የሌሎች ኤቲስቶችን ተፈጥሮአዊ አረዳድ ለሃይማኖታዊ ክርክር በሚያስኬድ እና የሀሳብ ለውውጥን በሚያመጣ መልኩ ለመማዘጋጀት ሞክሬየለሁ፡፡ የእኔን አስተሳሰብ ወደ ለየለት ሂሰኛ ያደረሱኝይህን መሰለ መፅሀፍት እና የኢንተርኔት መጣጥፎችናቸው፡፡ “The Internet is the modern-day World Book Encyclopedia. Everyone should have access to the Internet in their home, school, or public library” የሚለውን የአክቲቪስት Margaret Downey ምክር የተገበርኩት ይመስለኛል። ብዙ ደፋር ኤቲስቶች ህይወታቸውን አደጋ ላይ በመጣል ለምክንያታዊነት እየታገሉ ይገኛል፡፡ ተግሉም ህንፃ በማፈራረስ፣ በማሸበር፣ እና ነፃ አስተሳሰብን በመንፈግ አይደለም፡፡ ይልቁንስ አማኞች አይተው የሚፈሩት የእውነትን ማጅክ የሚያስረዱ መፅሀፈትን በመፃፍ እና ጹሁፎችን በእንተርኔት በማሰራጨት አንጅ፡፡ በግሌ የግሪክ ፍላስፎች፣ የአበው ሊቃውንት፣ የማርክስ፣ የፍሬድሪክ ኒቸ፣ (የአርዮስ?፣ የንስጥሮስ?፣ የሉተር?፣)የዘረዐ ያዕቆብ፣ የወልድ ህይወት፣ የዙምራ፣ (የበውቀቱ ስዩም፣ የዋለልኝ እምሩ፣ የብሩህ አለምነህ፣ የሃይለ ጊዮርጊስ ማሞ፣ የወርቁ ፈቀደ፣ የደረጀ ፀጋዬ) የኦሾ፣ የክሪስቶፈር ሂችን፣ የሳም ሃሪስ፣ የሪቻርድ ዶውኪንስ፣ የካርል ሳጋን፣ የማርሻል ብሬን፣የአያና አርሲ አሊ፣ የማይክል ሽርመር፣ የዳርዊን፣ የፍሮይድ፣ የጋሊሊዮ፣ የአንስታየን፣ የሀውክንግ ኧረ ስንቱን ሙህር ልጥራበቃ የነዚህ እና የሌሎች የሳይንስ እና የምክንያታዊነት አቀንቃኞችአደናቂ ነኝ፡፡ሞት ይርሳይ በፍቃዱ ሃይሉን ረሳሁት ምን ነበር ያለው፡- “የዓለም ሕዝቦች የቀለም እውቀት እና ከተሜነት እየተስፋፋ እና እየተመነደገ እየመጣ እንደመሆኑ መጠን፣ ከጥቂት መቶ ዓመታት በኋላ፣ አሁን ኢ-አማኒነት እብድነት እንደሆነው ሁሉ አማኒነት እብድነት መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡” አንተ ኢ-አማኝ ከሆንክ በቻልከው መጠን የቱንም መፅሀፍ ማንም ይፃፈው መቸም ይፃፍ ያለፍርሃት አንብብ እውነትን ካገኘህበት ተቀበል ካልመሰለህ ተወዉ፡፡ ብዙ ሰወች ከራሳቸው እምነት ውጭ ማንበብ ይፈራሉ፡፡ የሚገርመው እነዚ ሰወች የራሳቸውን ቀኖና እንኳ ቄሶቹ እንዲያውቁት እንጅ እነሱ እንዲገባቸው አይፈልጉም፡፡ ከተኙበት የሰመመን እቅልፍ ለመንቃት አያስቡም፣ ቀስቃሽም አይሹም፡፡ በአጭሩ ይህን መፅሀፍ በጃቸው ከነኩት ሰይጣን የሚያዛቸው የሚመስላቸው፣በመንጋ አስተሳሰብ የሚነዱ፣ ከእዉቀት ዛፍ እንዳይበሉ የተከለከሉ፣ ለራሳቸው ሀላፊነት የማይወስዱና ከጦር ይልቅ አስተሳሰብ የሚያስፈራቸው ናቸው፡፡ ስለ እምነታቸው እንዲሁም ስለ ፍልስፍን እና ሳይንስን ላለማወቅ ራሳቸውን ከጥበብ ያወሩ ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን ህይወታቸውን በአደራ ያስቀመጡ አስከሬኖች ናቸው፡፡ አስከሬን የት እንደተነሳ፣ በዙርያው ምን እየተፈፀመ እነደሆነ እና የት እነደሚሄድ አያውቅም፡፡

ሰው የትላንት ማንነቱን፣ የዛሬ ውሎ እና አዳሩን፣ እና የነገ ተስፋውን ከራሱ አሳልፎ ለ3ኛ ወገን ከሰጠ የቀረው ስጋ ብቻ ስለሆነ አስከሬን ማለቴ ቢከፋም አማራጭ የለኝም፡፡ ወይስ እንደ ደረጀ ፀጋየ “የስሜት የሹፌርነታቸውን ቦታ ለቀውለሸክም የተመቻቹ ጋሪዎች” ልበል። ለነገሩ እነዚህ ወቀሳዎች ደንበር ጥሰው ኢ-አማኝነትን ‘ሰነፎች’ ‘የገሃነብ ድጆች’ ‘የሰይጣን ልጆች’ ‘አረምውኔ ከሃዲዎች’ ‘አርዮሳዊያን’ ‘ለሶኦል የተጠበቁ’ ‘እራሳቸውን አምላኪዎች’ ‘666ቶች’ ‘እሪያዎች’ ‘አህዛብ’ እያሉ ለሚሳደቡ ሰባኪዎች ሲያንስ እንጅ አይበዛም።

ኢ-አማኞችን በተመለከተም ፍርሀት አለኝ። አንዳንድ የፀረ ሀይማኖት አስተሳሰብ አራማጆች በአንድ ጀንበር አማልዕክት ሙተው፣ ሀይመኖት ተወግዶ፤ቤተ-እምነቶች ሙዝየም ሁነው፤እና ዝግመታዊ ለውጥ ብቸኛው የተፈጥሮ አተረጓጎም ሁኖ ማየት የሚፈልጉ ጠባብ አተያይ ያላቸውን አሉ፡፡ ለምሳሌ ኮሚኒስት መንግስታት ሀይማኖት ካልጠፋ እድገት አይመጣምብለው በማሰባቸው በእምነቶች ላይ ዘመቻ ከፍተው ነበር፡፡ለእኔ ይህ አለማመንን ማምለክ ነው፡፡ ከማምለክ ስላልወጡ መሬት ገነት ሳትሆን ቀረች፡፡ ህልመቸውም ከሸፈ፡፡ መፍትሄዉ ይላል <ከማመን መጠራጠር ይሻላል>

‘ ‘ መፍትሄዉ በተለያየ አጋጣሚ የሀይማኖቶችን አካላዊ ላዜነት የተረዱና ሐይማኖቶችም ለሀገር እድገት ፀር መሆናቸዉን የተገነዘቡ ምክንያታዊ አሳቢወችን አደራጅቶ ህዝቡን የማስተማር ስራ እንዲሰሩ እድል መስጠት ነዉ። ታድያ እነኝህ ምክኒያታዊ አሳቢያን ማህበራዊ ሚድያ ላይ የምንፅፈዉን አይነት ሐይማኖትን የማዉገዝና የማንቋሸሽ ስራ እየሰሩ ህዝቡን የሚያስቆጡ መሆን የለባቸዉም።ምክንያቱም ህዝቡ ሐይማኖቱን ከጥንት ጀምሮ ጠብቆ ያቆየዉና ከህልዉናዉም ለይቶ ለማያየዉ በህዝቡ ኪፈለደበት አይገባም። ሌላዉ ቢቀር የኛ ህዝብ አለም ላይ ከክርስትናና ከእስልምና ዉጭ ሌላ ሐይማኖቶች መኖራቸዉን እንኳ የማያዉቅ አሳዛኝ ህዝብ ነዉ። ታድያ ይሄ ህዝብ ሳይንስንና ፍልስፍናን ቢፀየፍ ምን ይፈረድበታል? የሌላዉ አለም ህዝቦች እኮ ለሐይማኖታቸዉ ብዙም ቦታ የማይሰጡት በሐይማኖት ፋንታ ሳይንሳዊ እዉቀቶችን በደንብ በመማራቸዉና በማወቃቸዉ ነዉ። ስለዚህ የኛንም ህዝብ በባዶዉ ሀይማኖትህን ተዉ ማለት ሳይሆን ሳይንሳዊ እዉቀቶችን እያስጨበጡ በሐይማኖቱ ላይ ጥርጣሬን መፍጠርና ሀይማኖቱንም የሚተዉበትን መንገድ ማመቻቸት ነዉ የሚያዋጣዉ። ’ ’


ይህ የ<ከማመን መጠራጠር ይሻላል> ሀሳብ በ21ኛው ክ/ዘመን ላለን የድህ ሀገራት ቦርን አጌን (Born Again) ኤቲስቶች ጠቃሚ ምክር ይመስለኛል። እንደ ኢ-አማኝ ልናስበው የሚገባን ነገር ቢኖር የእውቀትን ዛፍ ፍሬ ወደ አለም መዝራት ነው፡፡ ከዚ ሌላ ሀይል መጠቀም ጅልነት ነው፡፡ በአራቱም የምድር ማዕዘኖች ከመቼውም ጊዜ በበለጠ መልኩ መረጃን መስጠትና መቀበል እንችላለን፡፡ ቀደም ሲል ኤቲስት ብትሆኑ ኖሮ የራችሁን ድምጽ ከመስማት በቀር አማራጭ አልነበርም፡፡ አሁን ግን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ በነፃነት በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ በድብቅ የሰውን ልጅ ጠፍንጎ ካሰረው አሉባልታ ነፃ መውጣታቸውን ልታውቁ ይገባል፡፡ ሳይንቲስት፣ፈላስፋ ወይም የስነ መለኮት ተመራማሪ መሆን ሳይጠበቅብን የሙህራኑን ምርምር በመረዳት ለዚህ ሰላማዊ ትግል የሚጠበቅብንን ማድረግ እንችላለን፡፡ በዚህ አብዮት የሚሳተፍ ከሰውነት የዘለለ ማዕረግ አይሰጠውም፡፡ ታምራት፣ ገድላት እና ድርሳናት አይፃፉለትም፡፡ ሽልማቱ በአደባባይ የሚሰጥ የኖበል ሽልማት አይደለም በጨለማ ለሚኖሩ ብርሃን በማካፈል የሚገኝ ደስታ እንጅ፡፡

**ተከታዩን ክፍል በሚቀጥለው እትማችን ያገኙታል።**


**ለማንኛውም አስተያየት**☞ abebawacc3368@gmail.com

ዮናስ ኃ/ማርቆስ

# አዲስ ለንባብ የበቁ መጽሀፍት




ርዕስ : ሰርሳሪ ተረከዞች
ደራሲ : የሺሐሳብ አበራ
ገፅ ብዛት : 246
ዋጋ : 130 ብር





ርዕስ : ሳፒያንስ
ትርጉም : አብዲሳ ቶሳ
ገፅ ብዛት : 408
ዋጋ : 200 ብር



ርዕስ : ብስጦሽ ቀዋጬ ቀዋጣሽ ቆር
ደራሲ : ታገል ሰይፉ
ገፅ ብዛት : 179
ዋጋ : 100 ብር




ርዕስ : የእውቀት አክፋሎተኛ
ደራሲ : ምንዳርአለው ዘውዴ
ገፅ ብዛት : 258
ዋጋ : 125 ብር




| | | |
|---|---|---|
| ርዕስ | : | መደመር |
| ደራሲ | : | አብይ አህመድ |
| ገፅ ብዛት | : | 280 |
| ዋጋ | : | 300 ብር |



| | | |
|---|---|---|
| ርዕስ | : | ስለ ትናንሽ አለሳዎች |
| ደራሲ | : | ዮናስ አ. |
| ገፅ ብዛት | : | 142 |
| ዋጋ | : | 100 ብር |


ኑ እናንብብ

ነጻ የአማርኛ ዲጅታል መጽሔት | Free amharic Digital Magazine

የኑ ክናንብብ ማህበራዊ ገጾችን ይቀላቀሉ !

እዚህ ይጫኑ

እዚህ ይጫኑ

# ምስጋና

በመጀመሪያ ሁሉን አድራጊ እና ፈጣሪ ለሆነው ለኡል እግዚአብሄር ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

በመቀጠል የ‹‹ኑ እናንብብ››ሀሳብን ስጀምር ጀምሮ እጅግ የበዛ እገዛው ላልተለየኝ ወንድሜ አብዲሳ ኮርሜ እንዲሁም ለእያሱ መስፍን ፣ የዲዛይን ስራዎቼን በማረም ላገዘኝ መምህር ዳንኤል ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

መጽሄቷ እንደመጀመሪያነቷ ከህዝብ ጋር እንድትተዋወቅ ላደረገልን ለ TIKVAH-ETH የቴሌግራም ቻናል፣መጽሔታችን ጋር አብሮ ለመስራት ለፈቀዳችሁ አምደኞቻችን ላቅ ያለ ምስጋናዬ ይደረሳችሁ፡፡

ጊዜያችሁን ሠጥታችሁ ላነበባችሁ ለእናንት አንባቢያን ምስጋናዬን እያቀረብኩ ሀሳብ አስተያየታችሁ አይለየን፡፡